# የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ በመጽሐፈ ስንክሳር፡ ይዘቱና የአጻጻፍ ስልቱ*

ሥርግው ገላው

## መግቢያ

ስለ መጽሐፈ ስንክሳር የተለያዩ ጥያቄዎች ይነሣሉ። ስንክሳርን ማን ጻፈው? መቼ ተጻፈ? ሃይማኖታዊ ሥነ ጽሑፍ ብቻ ነው ወይስ የኀለማዊ ሥነ ጽሑፍ ይዘትም አለው? ልብ ወለዳዊ ድርሰት ነው ወይስ ታሪካዊም? የሚሉት ከሚነሡት ጥያቄዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው። ይህ ጽሑፍ ስንክሳር መችና በማን ተጻፈ ለሚሉ ጥያቄዎች አጭር ማብራሪያ ካቀረበ በኋላ፡ ከፍ ብሎ ለተነሡት ሌሎች ጥያቄዎች ደግሞ የዛሬ 100 ዓመት አካባቢ የተጻፈ አንድ የስንክሳር ምንባብ በናሙናነት በማቅረብ መልስ ለመስጠት ይሞክራል።

የተመረጠው ምንባብ ስለ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንጉሠ ከፋ ወጎጃም ወልዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ (እንደ ስንክሳሩ አነጋገር ማለት ነው) የተጻፈው ነው። ታሪኩ ተጽፎ የተገኘው በደብረ ማርቆስ (ጎጃም) እና በብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ (አዲስ አበባ) አብያተ ክርስቲያናት ስንክሳሮች ነው። ምንባቡ የተመረጠው በሁለት ምክንያቶች ነው። አንዱ ምክንያት ታሪካቸውን በቅርብ በምናውቀው ሰው ላይ የተጻፈ በመሆኑ በሌሎች ምንጮችና በስንክሳር የተጻፈውን በማገናዘብ የስንክሳርን የታሪክ አመዘጋገብ ስልት ለመረዳት ያስችላል የሚል ሲሆን፥ ሌላው ምክንያት ደግሞ ንጉሡ የሞቱበትን 100ኛ ዓመት ለማዘከርም ነው።

እርግጥ ነው፡ በስንክሳሩ የተዘገበው የንጉሡ ታሪክ ሁሉንም የስንክሳር ምንባቦች ላይወክል ይችላል። ለምሳሌ ስለ መላእክት የተጻፉ ድርሰናትን አይወክልም። በሌላ በኩል ደግሞ ምንባቡ የሚወክላቸው ገድላትም አሉ።

ስለዚህ፡ ይህ ምንባብ በጭላንጭልነትም ቢሆን ስለ ስንክሳር የአጻጻፍ ስልትና ይዘት መጠነኛ ግንዛቤ ለማስተላለፍ ያስችላል ተብሎ ተመርጧል። ለናሙናነት ወደተመረጠው ስንክሳር ከመተላለፋችን በፊት ግን ስለ ራሱ ስለ ስንክሳር ምንነት መጠነኛ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል።

---

* ይህ ጽሑፍ ቀደም ሲል 14ኛው የኢትዮጵያ ጥናት ዓለም አቀፍ ጉባኤ "የመጽሐፈ ስንክሳር ይዘትና የአጻጻፍ ስልት ናሙናዊ ግምገማ" በሚል ርእስ ቀርቦ ከነበረውና ለሕትመት ከተሰጠው ጽሑፍ የተወሰደ መሆኑን እየገለጽን በአርእስቱም ሆነ በይዘቱ ለውጦች መደረጋቸውን እናሳስባለን።

## 1. ስለ መጽሐፈ ስንክሳር

ስንክሳር (*synaxarion*) የሚለው ግሪክኛ ቃል ወደ ግእዝና ወደ አማርኛ ሲተረጎም 'መድበለ መጻሕፍት' ማለት ይሆናል። ከመቸ ጀምሮ በሥራ ላይ እንደዋለ የሚያመላክቱ ትክክለኛ ማስረጃዎች የሉንም። ሆኖም በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለመኖሩ ዋቢ መጥቀስ ይቻላል (LThK[1] 1986: 1224-1225)።

ስንክሳር በቢዛንጥ፥ በቅብጥ፥ በአርመን፥ በሶርያና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛል። የመጀመሪያዎቹ ስንክሳሮች የቢዛንጥና የቅብጥ ሲሆኑ፥ የቀሩት ስንክሳሮች ከእነዚህ ተመልሰዋል (ዝኒ ከማሁ)።

ከግሪክኛው ስንክሳር በ1065 ዓ.ም. በሞተውና የአቶስ ገዳም አበ ምኔት በነበረው በጊዮርጊስ ስም የሚጠራው ስንክሳርና የሶርያ መለካውያን[2] ስንክሳር ተቀድተዋል። የኢትዮጵያና የሶርያ ስንክሳሮች ወደ ዐረብኛ ከተመለሰው የቅብጥ ስንክሳር መመለሳቸው ታውቋል። ይህ የዐረብኛ ስንክሳርም ቀደም ሲል በ1250 ዓ.ም. አባ ሚካኤል በተባለ የማሊግ ጳጳስ አማካይነት ከቅብጥ ወደ ዐረብኛ መተርጎሙን ፈረንሳይ አገር የሚገኝ አንድ የግእዝ ስንክሳር ይገልጻል (Budge, I: XIV; LThK, 1986፥1224-1225)።

ጥንታዊና ታዋቂ ከሚባሉት ስንክሳሮች ውስጥ አንዱ በ1240 ዓ.ም. የነበረውና እስራኤል የተባለው መነኩሴ የተረጎመው የአርመን ስንክሳር ነው። መነኩሴው ይህን ስንክሳር የአርመን ቅዱሳንንም ታሪክ ጨምሮና የአርመን ቤተ ክርስቲያንን ቀን አቆጣጠር ተከትሎ አዘጋጅቶታል። ከእነዚህ ስንክሳሮች በተጨማሪ በካቶልኮስ ጎርጎርዮስ 7ኛ (1295-1306) እና በጎርጎርዮስ ዘክህላት ስም የሚጠሩ ስንክሳሮች ይገኛሉ።

ስንክሳር ከመጽሐፍ ቅዱስ፥ ከያንዳንዱ ሐዋርያ፥ ሰማዕት፥ ጻድቅና መልአክ፥ ወዘተ. ገድላትና ድርሳናት ተውጣጥቶ ይጻፋል። ለዚህም ነው መድበለ ገድላት ወድርሳናት መባሉ።

'ገድል' ስሙ እንደሚያመለክተው ሰብአዊ ተፈጥሮ ያላቸው ቅዱሳንን (ለምሳሌ ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ሰማዕታት፥ ጻድቃን ወዘተ.) መንፈሳዊ ተጋድሎ በዋናነት ይዘግባል።

'ድርሳን' ደግሞ ሰብአውያን ያልሆኑ ቅዱሳን (መላእክት፥ ሰንበት) ሥነ ተፈጥሮ፥ ተልእኮ፥ ተራዳኢነት፥ ወ.ዘ.ተ. ይተረክበታል።

---

[1] Lexikon fuer Theology und Kirche

[2] ፈጻምያነ ፈቃደ ንጉሥ ለማለት። የኬልቄዶንን ጉባኤ 451 (ዓ. ም.) የተቀበሉት ዐዔውን (መርቅያንን) ፈርተው ነው በሚል ምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያኑ ይህንን ስም ሰጥተዋቸዋል።

'ተአምር' ሁለት ገጽታዎች አሉት። በአንድ በኩል፥ በገድልም በድርሳንም ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ይሆናል። ለምሳሌ ያህል ተአምረ ማርያምና ተአምረ ኢየሱስን ይጠቅሷል።

ስንክሳር የተዘጋጀው የቤተ ክርስቲያንን የቀን አቆጣጠር ተከትሎ ሲሆን፥ ዋና ዓላማውም በ365ቱ ዕለታት የሚታሰቡና የሚከበሩ ቅዱሳንን ታሪክ በአጭር በአጭሩ ማዘከር ነው። በአንድ ቀን ሁለት፥ ሦስትና ከዚያም በላይ በርካታ ቅዱሳን ታስበው ሊውሉ ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ስንክሳር በዐረብኛው ትርጉም ውስጥ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የጥቂት ኢትዮጵያውያን ቅዱሳንን ገድልም ይጨምራል። ሆኖም፥ የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ድርሻ ከሌሎች ጋር ሲተያይ ኢምንት ነው። አብዛኞቹ "ወበዛቲ ዕለት አዕረፈ . . . በረከቱ ትኩን ምስሌነ"፥ ማለትም፥ "በዚህ ቀን . . . ዐረፈ። በረከቱ ከእኛ ጋር ትሁን" ብለው ይደመድማሉ።

የኢትዮጵያን ቅዱሳንን ከውጭ የመጡ የኢትዮጵያ ቅዱሳን (ለምሳሌ ተሥዓቱ ቅዱሳን፥ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ) እና ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ቅዱሳን (ለምሳሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥ አቡነ ኢየሱስ ሞአ) ብለን በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። ከኢትዮጵያውያውን ቅዱሳን ውስጥ አንዳንድ የኢትዮጵያ ነገሥታት ይገኙባቸዋል። ለምሳሌ፣

1 አብርሀ ወአጽብሐ፣ ጥቅምት 4 ቀን
2 ዐፄ ካሌብ፣ ግንቦት 20 ቀን
3 ዐፄ ላሊበላ፣ ሰኔ 12 ቀን
4 ዐፄ ዳዊት፣ ህዳር 12 ቀን
5 ዐፄ ዘርዐ ያእቆብ፣ ጳጉሜ 3 ቀን
6 ዐፄ ናኦድ፣ ነሐሴ 7 ቀን
7 ዐፄ ልብነ ድንግል፣ መስከረም 5 ቀን
8 እቴጌ ሰብለ ወንጌል፣ ህዳር 25 ቀን
9 ዐፄ ገላውዴዎስ፣ መጋቢት 27 ቀን በስንክሳር ተዘግበዋል።

ይሁን እንጂ፥ በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ ታስበው እንደሚውሉ ከመጠቀሱ በቀር ታሪካቸው አልተጻፈም። በስንክሳር በመጠኑ ታሪካቸው ከተዘከረላቸው ነገሥታት ውስጥ ዐፄ ካሌብ፥ ዐፄ ላሊበላና ዐፄ ገላውዴዎስ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። እንደሚታወቀው፥ ዐፄ ካሌብ ታላቅ ጦር በመላክ የናግራንን (የየመንን) ክርስቲያኖችና ክርስትናን ከአይሁድ ለመጠበቅ ተከላክለዋል (ስንክሳር ግንቦት 20 ቀን)። ዐፄ ላሊበላም በርካታ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ አገልግሎት ሰጥተዋል። ዐፄ ገላውዴዎስ በበኩላቸው ቤተ ክርስቲያንን ከግራኝ ወረራ የተከላከሉ ከመሆናቸውም በላይ፥ ከኢአማንያን ጋር በመዋጋት ላይ ሳሉ የስቅለት ዕለት ሰማዕትነት ተቀብለዋል (ስንክሳር መጋቢት 27 ቀን)።

ከነገሥታቱ ሌላ፡ እንደ ቅዱስ ያሬድና እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያሉ ቅዱሳንም በመጠኑ ታሪካቸው ተጠቅሷል። እነዚህም ቅዱሳን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ታሪክ አላቸው። እስከ አሁን ያወሳነው ስለ አገር አቀፋዊ ስንክሳር ነው።

ይሁንና ከአገር አቀፋዊው ስንክሳር ለየት ያለ ታሪክ ያላቸው ሌሎች ስንክሳሮችም አሉ። የክልል (ጎጥ) ስንክሳሮች ልንላቸው እንችላለን። የክልል ስንክሳሮችን ከአገር አቀፋዊ ስንክሳሮች ለየት የሚያደርጋቸው ከአገር አቀፋዊው ስንክሳር በተጨማሪ የአካባቢያቸውን ቅዱሳን ገድል ጨምረው በመዘገባቸው ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የደብረ ማርቆስ (ጎጃም) ስንክሳር ነው። ይህ ስንክሳር የጎጃሙን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ገድል ጨምሮ በመዘገብ ከአገር አቀፋዊው ስንክሳር ይለያል። እንዲሁም፣ የብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ (አዲስ አበባ) ስንክሳር የዚሁ ስንክሳር ቅጅ በመሆኑ፣ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ገድል ይዟል። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ገድል ከተጠቀሱት ስንክሳሮች በቀር በሌሎች ስንክሳሮች አይገኝም። እነዚህ የክልል ስንክሳሮች ከአገር አቀፋዊው ስንክሳር መለየታቸው በዚህ ነው።

ይህ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ በአገር አቀፋዊው ስንክሳር ባይገኝም በመደበኛው የስንክሳር የአጻጻፍ ስልት ስለተጻፈና የንጉሡንም ገድል ከሌሎች ምንጮች አገናዝቦ ለመመርመር የሚቻል በመሆኑ፣ ይህንኑ ስንክሳርና የአጻጻፍ ስልቱን መመርመር ለጠቅላላው ስንክሳር ይዘትና የአጻጻፍ ስልት ጥናት አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም፣ በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ገድል ላይ የተጻፈውን ይህንን ስንክሳር ዝቅ ብለን እንመረምራለን።

ከዚያ በፊት ግን፣ ለዋናው ሥራችን በር ከፋች ይሆን ዘንድ፣ የዘጋቢውን የመልአከ ፀሐይ ተገኘንና የተዘጋቢውን የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ታሪክ በአጭር በአጭሩ እንመልከት።

1.1. የስንክሳሩ ዘጋቢ የመልአከ ፀሐይ ተገኘ አጭር ታሪክ

መልአከ ፀሐይ ተገኘ ጎጃም ውስጥ በብቸና አውራጃ፣ በጥላትግን ወረዳ፣ ልዩ ስሙ ወንዳሳ ቁስቋም በተባለ ቀበሌ ተወለዱ። ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፣ በተለይም ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍትን፣ የተማሩ ሊቅ ከመሆናቸውም በላይ ንድፍ የመንደፍና እቅድ የማውጣት ልዩ ተሰጥዎ ነበራቸው።

መልአከ ፀሐይ ተገኘ፣ ደብረ ማርቆስ ሲጀመር ጀምሮ ሥርዐተ ደብሩን ያጠኑና ያቀኑ ከመሆናቸውም በላይ፣ በትርፍ ጊዜያቸውም በርካታ መጻሕፍትን ጽፈው እንደነበር ይነገራል። ከጻፏቸው መጻሕፍትም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡

1 በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍትንና የሚገኙባቸውንም ቦታዎች የሚያሳይ ዝርዝር፡
2 የኢትዮጵያ ሊቃውንትና ደጋግ ሰዎች ስም ዝርዝር፡
3 የሊቃውንት ቅኔ፡

4 የኢትዮጵያንና የስንደቅ አላማውን ታሪክ የሚገልጽ ጽሑፍ፡
5 መጽሐፈ ግጻዌ፡
6 ከአባ ማርቆስ ጋር በመሆን ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ የተረጎሚቸው ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፡
7 የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ፡፡

እንዲሁም ከተጠቀሰው የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ በተጨማሪ ይህንን ገድላቸውንም በደብረ ማርቆስ ስንክሳር አስገብተው ጽፈዋል።

1.2 የስንክሳሩ ተዘጋቢ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አጭር የሕይወት ታሪክ

የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ታሪክ መልአከ ፀሐይ ብሩ፡ መልአከ ፀሐይ ተገኘና አለቃ ተክለ ኢየሱስ መጻፋቸው ይነገራል። ከዚህ ውስጥ የሌሎች ጸሐፊዎች ሰነዶች ያልተገኙ ሲሆን፡ የአለቃ ተክለ ኢየሱስ ሰነድ፣ ባይታተምም፣ በተለያዩ አብያተ መጻሕፍትና ግለሰቦች እጅ ይገኛል። ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ በተባለውና ባልታተመው መጽሐፋቸው የንጉሥ ተክሎ ሃይማኖትን ታሪክ እንደሚከተለው ዘግበውታል።

የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አባት ደጃች ተሰማ ናቸው። ደጃች ተሰማም የዳሞቱ ገዥ የደጃች ጎሹ ዘውዱ ልጅ ናቸው። ደጃች ጎሹም የታላቁ ራስ ኃይሉ የልጅ ልጅ መሆናቸው ይታወቃል።

በሌላም በኩል የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እናት ወይዘሮ ምእላድ ይባላሉ። አገራቸውም ማቻከል ውስጥ ትቤ አቦ ነው ይባላል (66)።[3]

ተክለ ሃይማኖት በመጀመሪያ አዳል ይባሉ ነበር። ልጅ አዳል መቼና የት እንደተወለዱ በትክክል የሚያመለክት ጽሑፍ አልተገኘም። ሆኖም በ1843 ዓ.ም. አካባቢ ደጋ ዳሞት ውስጥ፣ ጣሜ ጊዮርጊስ ከተባለው ደብር መወለዳቸውን የሚናገሩ ሰዎች አሉ (ሊቀ ካህናት መርዓዊ የብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ካህንና ታሪክ አዋቂ)።

የልጅ አዳል አባት ደጃች ተሰማ ጎሹ በ1845 ዓ. ም. በዐፄ ቴዎድሮስ ተማርከው አርማጭሆ አርባ አምባ ላይ (66) እንደተጋዙ ስለሞቱ የልጅ አዳል እድገት በቅርብ ዘመዳቸው በደጃች ተድላ ጓሉ ቤት ነበር። በዚህ ወቅት ከደጃች ተድላ ልጅ ከልጅ ንጉሤ ጋር ሁነው በጅበላ ከሊቀ ካህናት ወርቄ ዘንድና ከዚያም በፊት በደንበጫ ከፈንታ ወልደ ሴም ዘንድ የቤተ ክህነት ትምህርት መማራቸው ታውቋል (66)።

አዳል ከአሳዳጊያቸውና የቅርብ ዘመዳቸው ከሆኑት ከደጃች ተድላ ጓሉ ጋር ተቀያይመው ገና በወጣትነታቸው ሸፈቱ (66)፡፡ የሸፈቱት በወጣትነት መንፈስ

[3] ያለ ምንም መግለጫ በቅንፍ ( ) ውስጥ የተመለከቱ ቁጥሮች በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የሚገኘውን ያልታተመውን የተክለ ኢየሱስን የኢትዮጵያ ታሪክ ገጽ ቁጥር ሲያመለክቱ፣ (ቁ ) ተብለው የተመለከቱት ቁጥሮች ደግሞ ከዚህ ጋር አባሪ ሆኖ የቀረበውን ስንክሳር ቁጥሮች ያመለክታሉ። በነገራችን ላይ ስንክሳሩን በቁጥሮች የከፋፈለው የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ነው።

በፈጸሙት ጥፋት ቅጣት ይፈጸምብኛል በሚል ፍርሃት ቢሆንም፣ ሽፍትነቱ ባላሰቡት መንገድ የወደፊት እድላቸው በር ከፋች ሆኖላቸዋል:: ምንም እንኳን አጎታቸው ደጃች ተድላ ከሞቱ በሁዋላ ከወራሻቸው ከደስታ ተድላ ጋር ታርቀው የገቡ ቢሆንም፥ ሹመት አነሰኝ በማለት እንደገና ሽፍትነታቸውን ቀጠሉ (79)::

በረሃ እያሉም በቴዎድሮስ ጊዜ በሽፍትነት ይታወቁ የነበሩት ዋግ ሹም ጎበዜ በጉልበታቸው ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ጎጃምን ለማስገበር ብቅ ሲሉ ብአድራጎታቸው የተበሳጩት ራስ ደስታ ለተክለ ጊዮርጊስ አልታጠቅም አሉ:: በተቃራኒው ባላምባራስ አዳል በፀረ ደስታ አቋማቸው ከበረሃ ገስግሰው ለተክለ ጊዮርጊስ አደሩ :: ተክለ ጊዮርጊስም የደስታ ግማሽ ግዛት የሆነውን ዳሞትን ለአዳል በመቸር ሂሳባቸውን አወራረዱ (80)::

ገና የተክለ ጊዮርጊስ እግር እልፍ ሳይል ደጃች አዳል ሌላ በለስ ቀናቸው:: ለተክለ ጊዮርጊስ አልታጠቅም በማለት ከራስነት ወደ ሽፍትነት ወርደው የነበሩትን የቅርብ ዘመዳቸውን ደስታን ማርከው ለዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ሰለባ ጧሏቸው:: ተክለ ጊዮርጊስም በዳሞት ላይ ጎጃምን መረቁላቸው(80):: ከቅርብ ወራት በፊት ባላንባራስ የነበሩት አዳል ራስ ሆኑ::

ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ የተንቤኑን ሽፍታ በዝብዝ ካሳን ሲወጉ ዐፄው ተማርከው ሽፍታው አፄ ይሆናል የሚል ግምት ያልነበራቸው ራስ አዳል 500 የጎጃም ጦር በመላክ ለዐፄው ድጋፍ ሰጡ (81):: ይህ ስሌታቸው ስህተት መሆኑን ሲረዱ ግን ለሚቀጥለው ሽፍትነት መዘጋጀት ነበረባቸው::

በዝብዝ ካሳ ዐፄ ዮሐንስ እንደሆኑ የተክለ ጊዮርጊስ መንግሥት ርዝራዥ የሆነውን የራስ አዳልን ግዛት ማስወገድ የመጀመሪያ ሥራቸው አደረጉት:: ስዚህም አዳል ቀደም ሲል አቁስለው ለዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ግዞት አሳልፈው ሰጥተዋቸው የነበሩትን ራስ ደስታን ፈትተው ወደ ጎጃም ገሰገሰ:: ዮሐንስ ጎጃም እንደደረሱ ሁለቱ ራሶች ቦታ ተቀያየሩ:: ደስታ ወደ ዳሞትና ጎጃም መስፍንነታቸው አዳልም ወደ ሽፍትነቱ::

ቢሆንም፣ አዳል ከራስ ደሰታ የተሻለ ታጥቀው ነበር:: ባሻ ውድነህ[4] በሰሩላቸው መድፍ ራስ ደስታን ገድለው ማንነታቸውን ለዮሐንስ አሳዩ:: ዮሐንስ ነገሩ አላማራቸውም:: ከኃይል ይልቅ ፖለቲካዊ መፍትሄ የተሻለ ሆኖ አገኙት:: በመሆኑም፣ በጳጳሱ በአባ አትናቴዎስና በጎጃሜው በእጨጌ ቴዎፍሎስ አደራዳሪነት፣ አዳል የዮሐንስን ዐፄነት፣ ዮሐንስም የአዳልን የዳሞትና ጎጃም መስፍንነት አውቀው አዲሲቷን ኢትዮጵያ በጋራ ለመገንባት ተስማሙ::

---

[4] ባሻ ውድነህ የደጋ ዳሞት አዋሳኝ የሆነው የቢቡኝ ወረዳ ተወላጅ ናቸው:: ዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ በሚያሠሩበት ጊዜ ባሻ ውድነህ ከፈረንጆች ጋር በመሆን የመድፍ ሥራ ተምረዋል:: ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው ለራስ አዳል አድረው መድፍ ከሠሩ በኋላ ራስ አዳልና ራስ ደስታ ሲዋጉ፣

ውዬ የኮሶ እሸት

በሠራው ገዳይ እንደመለኮት

ብለው የሠሩትን መድፍ ሲተኩሱ የደጃች ደስታ በቅሎ ደንግጣ ተንበረከከች ይባላል:: ወዲያውም ከሳ ምንተስኖት የሚባል ወታደር "ይህ ልማደኛ ሞቶ መነሳቱን ያውቅበታል" ብሎ የራስ ደስታን አንገት በስለት መቁረጡ ተጽፏል (82)::

እውነትም ዮሐንስና አዳል ቀስ በቀስ እየተቀራረቡና እየተግባቡ ሄዱ፡፡ ዐፄ ዮሐንስ የአማራ ተቀናቃኞቻቸውን፣ ይልቁንም ይፈሩዋቸው የነበሩዋቸውን የምኒልክን የኃይል ሚዛን ለመጠበቅ በራስ አዳል ሲጠቀሙ፣ ራስ አዳልም በበኩላቸው ዘመዶቻቸውን ለመጫንና ግዛታቸውንም እስከ ምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያ ለማስፋፋት፣ ሥልጣናቸውንም ከራስነት ወደ ንጉሥነት ከፍ ለማድረግ በዮሐንስ ተጠቅመዋል፡፡ በመሆኑም ራስ አዳል ከምኒልክ ጎን ለጎን በኢትዮጵያ ብቸኛው ገናና መስፍን ሆነው ብቅ አሉ፡፡

በዚሁ መሠረት ዐፄ ዮሐንስ ጥር 13 ቀን 1873 ዓ.ም. የምኒልክን የሸዋ ንጉሥነት ሲያፀድቁ፣ ራስ አዳልንም ንጉሠ ከፋ ወጎጃም በማለት ደብረ ታቦር ላይ አንግሠዋቸዋል፡፡ ንጉሠ ከፋ ወጎጃም የተባሉት ቀደም ሲል ኩታይንን፣ ጉንሩን፣ ጂማን፣ ገነቴን፣ ሁሮን፣ አምሮን፣ ጂዳን፣ ሊሙን፣ ጨልያን፣ ከፋን፣ ኢሉባቦርን፣ ኩሎኮንታን፣ ጊሚራን አቅንተው ስለ ነበር ነው፡፡

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከፖለቲካ ይልቅ ሐቀኝነትንና እምነትን፣ በጦር ሜዳም ቢሆን ከታክቲክ ይልቅ ድፍረትንና እልህን ያዘወትሩ ነበር፡፡ በተለይ፣ ሃይማኖት አጥባቂ ስለ ነበሩ፣ በጎጃም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጻድቅና ቅዱስ ይታሰባሉ፡፡ ንጉሡ ባረፉበት በጥር 3 ቀን የሚነበበውና ቀጥሎ የምንመለከተው የደብረ ማርቆስ ስንክሳርም በዚሁ መንፈስ የተጻፈ ነው፡፡

## 2. የስንክሳሩ የአጻጻፍ ስልት

እያንዳንዱ ስንክሳር መግቢያ፥ ዋና ክፍልና መደምደሚያ አለው።

### 2.1. መግቢያ

መግቢያው "ወበዛቲ ዕለት አዕረፈ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንጉሠ ከፋ ዘተሰምየ ርቱዐ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ወልዱ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ" (በዚህ ቀን ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ቀናተኛ የሆነውና የወንጌላዊው ማርቆስ ልጅ የተባለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አረፈ) ወይም "ወበዛቲ ዕለት ተዝካረ በዓሉ ለ..." (በዚህ ቀን የ... በዓል መታሰቢያ ነው) በማለት ታሪኩን ይጀምራል።

በመሠረቱ የሕይወት ታሪክ እንደ ራሱ እንደ ሕይወት በልደት ተጀምሮ በሞት ይፈጸማል። በስንክሳር የአጻጻፍ ስልት ግን እንደዚህ አይደለም። የስንክሳር ታሪክ እንደ ራድዮ ዜና እወጃ ወይም እንደ ዕለታዊ ጋዜጣ በአርእስተ ነገሩ ይጀምራል። ከዚያም ወደ ታሪኩ ይመለሳል። "በዚህ ዕለት .... አረፈ" ካለ በኋላ የሕይወት ታሪኩን እንደ መጀመር ማለት ነው። ይህም "በዚህ ቀን ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ቀናተኛ የሆነውና የወንጌላዊው ማርቆስ ልጅ የተባለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አረፈ" (ቁ. 1) ካለ በኋላ፣ "የዚህ ቅዱስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አባትና እናት የቤተ መንግሥት ተወላጆች ነበሩ። እነሱም በጎጃም ተወለዱ" (ቁ.2) በማለት ወደ ኋላ ተመልሶ ታሪኩን ይጀምራል።

## 2.2. ዋና ክፍል

በጽሑፉ ዋና ክፍል የባለገድሉ (የተደረሹ) የሕይወት ታሪክ ለገድሉ መግቢያ ያህል በአጭሩ ይወሳል። በአብዛኛው ደግሞ መንፈሳዊ ተጋድሎው፥ ስለ እሱ የተነገሩ ትንቢቶችና የተፈጸሙ ተአምራት ሰፋ ተደርገው ይተነተናሉ። ሆኖም ከዚሁ ጋር የእሱና የሌሎችም ዓለማውያንና ተጨባጭ የሆኑ ታሪኮች አብረው ሊመዘገቡ ይችላሉ። ስለሆነም፡ የስንክሳሩን ዋና ክፍል ዓለማዊ ታሪክና መንፈሳዊ ገድል ብሎ በሁለት መክፈል ይቻላል።

በዓለማዊው ታሪክ ሥር በዚያን ዘመን ቴዎድሮስ (ቁ.4 )፥ ተክለ ጊዮርጊስ (ቁ.6)፥ ዮሐንስ (ቁ.7)፡ እና ምኒልክ (ቁ.14) የተባሉ ዐፄዎች በቅደም ተከተል በኢትዮጵያ መንገሣቸውና ተክለ ሃይማኖትም ከተጠቀሱት ዐፄዎች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተጠቅሷል። የተክለ ጊዮርጊስ፥ የዮሐንስና የምኒልክ የኢትዮጵያ ነገሥተ ነገሥታት መሆንና ተክለ ሃይማኖትም በተክለ ጊዮርጊስ ራስ አዳል ተብለው የጎጃምና ዳሞት ገዥ መሆናቸው (80)፥ በዮሐንስ ንጉሠ ከፋ ወጎጃም መባላቸውና (83) ይሄውም እንደገና በምኒልክ መጽደቁ በታሪክ የታወቀና የተረጋገጠ ነው (ተክለ ጻድቅ፣ 1936፣ 93)።

ስለዚህ፡ ይህንን አስመልክቶ በስንክሳሩ የተጻፈው እውነት እንደሆነ ይታያል። በመሆኑም፣ ስንክሳር ከመንፈሳዊ ገድል በተጨማሪ ተጨባጭና ተዳሳሽ ታሪኮችንም ሲያስተላልፍ ይታያል። የስንክሳር ዋነኛ ክፍሉ መንፈሳዊ ገድሉ ነው።

መንፈሳዊውን ገድል "ታሪካዊ" እና "እምነታዊ" በማለት በሁለት ሊከፋፈል ይቻላል። ታሪካዊ መንፈሳዊ ገድል የምለው ስለ ደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አተካከልና ግንባታ (ቁ.12)፥ በጎጃም፥ በከፋና በሌሎችም ኢአማንያን አካ... ስለተሠሩት አብያተ ክርስቲያናትና ለእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት፥ በተ... ለደብረ ማርቆስ፥ ስለተሰጡት ርስተ ጉልቶች የሚናገረውን ክፍል ነው (ቁ.... ነው። እነዚህ ታሪኮች ተጨባጭና ተዳሳሾች ስለሆኑ በታሪክ ፊት ተቀባይነት አላ... ለምሳሌ፣ የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በተክለ ሃይማኖት መተከሉና አ... ሦስት መቅደሶች ያሉት መሆኑ የሚታወቅና ዛሬም የሚታይ ነው (87፣ 107፣ 1... ...ዩ )

በሌላ በኩል፣ ንጉሡ ሌሎች በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን ማሠራታቸው፥ (108) ለአብያተ ክርስቲያናቱም ስፍር ቁጥር የሌለው ርስት ጉልት መስጠታቸው፥ ይሄውም እንቅስቃሴያቸው በመኳንንቱ ዘንድ ነቀፋን እንዳስከተለባቸው (ቁ.16 ) በሌሎችም ታሪኮች ተጽፎ ይገኛል። ስለዚህ፥ ሁሉም ተጨባጭነትና እውነትት እንዳላቸው እናያለን። ሌላው የስንክሳር ክፍል እምነታዊ ገድሉ ነው።

እምነታዊ ገድል የምለው በምንባቡ የተጠቀሱትን፣ እንደ ትንቢትና ምልክት ያሉትን ነው። ለናሙናነት በቀረበው ምንባብ መሠረት፥ ዐፄ ቴዎድሮስ (ቁ. 4)፥ አባ ማርቆስ (ቁ. 5) እና አባ ዘውገ መላእክት (ቁ.10) የተባሉ መነኰሳት ስለ አዳል ንጉሥነትና ስለ መንቆረር የወደፊት መዲናነት አስቀድመው ትንቢት ተናግረዋል። ከዚህም በላይ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ርብ ታዝዞላቸዋል (ቁ 8)። ቀስተ ደመና ወርዶላቸዋል (ቁ.17)። ለሥርዐተ ቀብራቸው ዝግጅት ቅዱስ አፈርና

ቅዱስ ውሀ ከቅድስት ሀገር (ኢየሩሳሌም) በሕይወታቸው ፍጻሜ በተአምር ደርሶላቸዋል (ቁ.21)።

ጸሓፊው ቀደም ሲል ዓለማዊና ታሪካዊ መንፈሳዊ ታሪክ ባልነው ክፍል ያልሆነ ነገር (ውሸት) ስላልጻፉ እነዚህም ነገሮች ተፈጽመው ይሆናል። ነገር ግን ይህ ዐይነቱ ታሪክ ለአማኞች የሚነገር እንጂ ለአንባቢው ሁሉ የሚረዳ ባለመሆኑ እምነታዊ እንጂ ታሪካዊ ልንለው አንችልም።

## 2.3. መደምደሚያ

የስንክሳር የመጨረሻው ክፍል መደምደሚያው ነው። ስንክሳር አጫጭር የቅዱሳን ገድል ቢሆንም፥ መደምደሚያው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች ቀብር ላይ ከሚነበበው የሕይወት ታሪክ መደምደሚያ ይለያል። የቀብር የሕይወት ታሪክ መደምደሚያ "ነፍሳቸውን ይማርልን" ወይም "ነፍሳቸውን በአብርሃምና በይሥሐቅ አጠገብ ያኑርልን፡ ኀዘንተኞቹን ያጽናናልን" በማለት ይደመድማል። ስንክሳር ግን "በረከቱ ትኩን ምስለ..." (ማለትም፣ "በረከቱ ከ...ጋር ትሁን") (ቁ.23)፥ በማለት ይደመድማል። ከተነበበው ገድል እንደምንረዳው ባለ ገድሉ እንደጸደቀ የታወቀ ነው። ስለዚህ እሱ ለእኛ ለሕያዋን ይጸልያል እንጂ እኛ ለእሱ አንጸልይም። መጽሐፍ "ሕያዋን ይስእሉ በእንተ ሙታን"፡ ማለት "ሕያዋን ስለሙታን ይለምናሉ" ቢልም "በእንተ ቅዱሳን" አላለም። ስለዚህ ለእሱ መጸለይ ሳያስፈልግ የእሱ በረከት፥ ረድኤትና አማላጅነት ከእኛ ጋር እንዲሆን በመመኘት ይፈጽማል። ይህም ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን አማላጅነት መሠረታዊ እምነት የመነጨ መሆኑ ነው።

የመደምደሚያው ሌላው ክፍል ዓርኬው ነው። ዓርኬ አምስት ስንኞች ብቻ ያሉት ግጥም ነው። "ሰላም ለ...." በማለት ይጀምርና በምንባቡ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን አንኳር አንኳር ታሪኮች፣ በተለይም ትንቢቶችንና ተአምራትን፣ በግጥም በመድገምና ቅዱሱን በማወደስ ይፈጸማል (ቁ.24 )። በመሆኑም ዓርኬ ቀደም ሲል የተነገረውን በከፊል፡ ወይም ከገድሉ ውስጥ አንዱን ክፍል በመድገም ለገድሉ አጽንዖት ከመስጠቱም በላይ፣ አገላለጹ በግጥም መልክ በመሆኑ ሐሳቡ እንዳይረሳ ያደርጋል።

# 3. የስንክሳሩ ትንታኔ

## 3.1. ታሪክ (ዓለማዊ)

በዚህ ስንክሳር ውስጥ ዓለማዊ ታሪክ ከመንፈሳዊ ገድል ጋር ጎን ለጎን ሲተላለፍ እናስተውላለን። እርግጥ የስንክሳሩ ዋና ዓላማ በጸሓፊው አመለካከት በመንፈሳዊ ተግባራቸው ወደ ቅዱስነት ደረጃ ከፍ ያሉትን ንጉሥ መንፈሳዊ ገድል መዘገብ ነው። ይህም "ወለዝንቱ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ኮኑ አቡሁ ወእሙ እምእዝማደ ቤተ መንግሥት" ("የዚህ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት አባቱና እናቱ ከቤተ መንግሥት ወገን ናቸው") (ቁ.2) በማለት "ቅዱስ" የሚለውን ቃል በመቀጸሉና "ሰላም ለተክለ ሃይማኖት ውዱስ (ለተመሰገነው ተክለ ሃይማኖት ሰላምታ ይገባል")

(ቁ.24) በማለቱ ይታወቃል። ይሁን እንጂ፥ አበው "ያለ ሥጋ ነፍስ አትቆምም" እንዲሉ፥ መንፈሳዊው ከቁስ አካላዊው፥ ሃይማኖታዊውም ከሥጋዊው ተለይቶ ብቻውን መቆም አይችልም። ነፍስና ሥጋ አንድም ሁለትም ናቸው። ነፍስና ሥጋ የተዋሐዱትን ያህል ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ታሪክም የተዋሐዱ ናቸው። በታሪክም መንፈሳዊውና ቁስ አካላዊው፥ ሃይማኖታዊውና ሥጋዊው የተሳሰሩና የተቆራኙትን ያህል መንፈሳዊውን ለማዘከር ዓለማዊውንም መዳሰስ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር የዚህ ገድል ዘጋቢ ከመንፈሳዊው ዘገባቸው በተጓዳኝ ዓለማዊውንም ታሪክ ዳስሰዋል። ይህም የማይዳሰሰውንና ረቂቁን መንፈሳዊ ገድል ለማስረዳትና ለማስረገጥ ተዳሳሹንና ግዙፉን ታሪክ መጥቀስ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ለምሳሌ፥ ዘጋቢው እንደ ዋና ጉዳይ አድርገው የወሰዱትን የዐፄ ቴዎድሮስን ትንቢት ለመጥቀስ "በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ ወደ ምድረ ጎጃም ደረሰ። ወደዚያ ንጉሥ ከተማም ገባ" (ቁ. 4) በማለት ትንቢቱ ተነገረበት የተባለውን ቦታና ሰዓት፥ ትንቢቱንና፥ በእሳቸው እምነት፥ ነቢዩንም መጥቀስ አስፈልጓቸዋል። ይህም የረቀቀውን በጎላው የማይዳሰሰውን በሚዳሰሰው አጉልቶ ለማሳየትና ለማስረዳት ሆን ብለው ያደረጉት ነው። ሆኖም የጸሓፊው ዋና ዓላማ መንፈሳዊው ገድል እንጂ ዓለማዊው ስላይደለ ዓለማዊውን ታሪክ ባንድ ዐረፍተ ነገር ወይም ሐረግ ብቻ ነካ አድርገው ሲያልፉት ይታያል። ለምሳሌ፥ "መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ በሞቱ ጊዜ ተክለ ጊዮርጊስ ነገሠ። ይህንንም ልጅ ለጎጃም መስፍን አድርጎ ሾመው" (ቁ. 6) በማለት ለቴዎድሮስ ሞትና ለተክለ ጊዮርጊስ መንገሥ አንድ አረፍተ ነገር ብቻ በቅቷቸዋል። ለተክለ ጊዮርጊስ መሻርና ለዮሐንስ መውደቅም እንዲሁ። "ከዚህ በኋላ ተክለ ጊዮርጊስ ተሻረ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስም ነገሠ" (ቁ.7) በማለት ይቀጩታል። ምክንያቱም ዓላማቸው ስንክሳር እንጂ ዜና መዋዕል (ታሪክ) መጻፍ አይደለምና።

ከፍ ብሎ እንደታየው የተክለ ጊዮርጊስ ድል መሆንና የዮሐንስ ድል አድርጎ መንገሥም በሁለት አረፍተ ነገሮች ብቻ ተገልጿል። አገላለጹም ድል በመሆንና በማድረግ መንፈስ ሳይሆን የአንደኛውን መሻርና የሌላውን መንገሥ በደፈናው በመንገር ነው። ይህ የሆነው ከፍ ሲል እንደተገለጸው ዋና ግባቸው የተክለ ሃይማኖትን ገድል መዘከር እንጂ ዜና መዋዕል መጻፍ ባለመሆኑ ነው። ሌላ ምሳሌ እንጨምር።

> "ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም ፈቃዱን እንዲፈጽም ፈቃዱንም አብልጦ እንዲያደርግ በተመለከተ ጊዜ ያነግሠው ዘንድ ወደ ደብረ ታቦር ጠራው (አንቀጽ 9)....ይህንንም መልእክት ከሰማ በኋላ ወደ ደብረ ታቦር ሄደ። ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም በከፋ፥ በጎጃምና በሌሎችም ኢአማናውያን አገሮች አነገሠው" (ቁ.11)።

ገድላቸውን ሊዘግቡላቸው የተነሡትን ንጉሥ የንግሥና ታሪክ እንዲህ በጥቂት አረፍተ ነገር ብቻ መግለጻቸው ለዓለማዊ ታሪካቸው ምንም ያህል ትኩረት አለመስጠታቸውን ያሳያል። በተጨማሪም፥

> ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም ባረፈ ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነገሠ። እሱም ኃያልና ታጋሽ፥ ሁልጊዜም ጥፋትን የማያመጣ

ነበር። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትንም እጅግ ወደደው። እንደገናም አነገሠው። የመንግሥት ዘውድንም ሰጠው (ቁ. 14)

በማለት ሁሉም ዓለማዊ ታሪክ አጠር አጠር እየተደረገ ለመንደርደሪያ ያህል ተወስቷል።

3.2. ገድል (መንፈሳዊ)

የምንባቡን መንፈሳዊ ገድል በሁለት ልንከፍለው እንችላለን፤ የሚዳሰስ መንፈሳዊ ገድልና እምነታዊ መንፈሳዊ ገድል በማለት።

3.2.1 የሚዳሰስ መንፈሳዊ ገድል (አብያተ ክርስቲያናት ማሠራት፣ ክርስትናን ማስፋፋት ወዘተ.)

በተጨባጭ መንፈሳዊ ገድል ሥር ንጉሡ ያሠሩት የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያንና ለአብያተ ክርስቲያናት የፈጸሙት ትሩፋት ይጠቀሳል። ለምሳሌ፤

> የወንጌላዊውን የማርቆስን ታቦትም ወሰደ። ያማረች ቤተ ክርስቲያንን ሠራ። እስክንድርያዊው መቃርዮስ በሮምና በቁስጥንጥንያ መካከል ባሠራትና ወንጌላዊው ማርቆስ ብዙ ታምራት ባደረገባት ቤተ ክርስቲያን አምሳል ሦስት መቅደሶችን አደረገላት። የቀኙን የአባታችን የወንጌላዊው የማርቆስ መቅደስ አለው። መካከለኛውን በአምላካችን በሥሉስ ቅዱስ ስም ሰየመው። የግራውን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ሰየመው (ቁ. 12)።

ከንጉሡ የንግሥና ታሪክ ይልቅ የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ሰፋና ዘርዘር ብሎ ተገልጿል፤ ጉዳዩ መንፈሳዊ ነውና። የቤተ ክርስቲያን ርስተ ጉልትም እንዲሁ በተሻለ ሁኔታ፤

> በኢአማናውያንና በክርስቲያን አገሮች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሠራ። በመንግሥቱም ውስጥ ላሉት አድባራት ያላደረገው በጎ ነገር የለም። ይልቁንም ለደብረ ማርቆስ። ብዙ ጉልቶችንም ሰጠው። ብዙ አገሮችንም መስጠት ባበዛ ጊዜ ከአማካሪዎቹ አንዱ ከአንተ በኋላ የማይሆነውንና የማይጸናውን ለምን ታበዛለህ? አለው። እሱም እኔ በዘመኔ ለቤተ ክርስቲያን እሰጣለሁ ለመንግሥቴ ጥቅም የሚሆነውንም ለቤተ ክርስቲያን እተዋለሁ። ካለፍኩ በኋላ ባይጸና ግን በሕይወቴ ያደረግሁትን እግዚአብሔር ዋጋዬን አያጠፋም አለው (ቁ.15÷16)።

3.2.2 እምነታዊ (የማይዳሰስ) ገድል (ታምራት÷ትንቢቶች)

እምነታዊ ገድል የምለው መንፈሳዊም ሆኖ ከታሪክ አንጻር ለአማኞች ካልሆነ በቀር ለታሪክ ሰዎች ሊዳሰስና ሊታመን የማይችለውን ክፍል ነው። ለምሳሌ ያህል÷ በዚህ ስንክሳር ትንቢቶችና ምልክቶች ትልቁን ድርሻ ይዘዋል። በመንፈሳዊ አመለካከት÷ ይልቁንም በቀደመው መንፈሳዊ አስተሳሰብ÷ ትንቢቶችና ምልክቶች ትልቅ ግምት ይሰጣቸዋል። የጥንት እስራኤላውያን ነቢያት እንዳሏቸው ሁሉ÷ በኢትዮጵያም÷ ነገሥታትና ባሕታውያን ትንቢት ሊናገሩ ይችላሉ። ኀላፍያቱና መጻእያቱ ይታይዋቸዋል የሚል አስተሳሰብ ነበር። ሳኦል÷ ዳዊትና ሰሎሞን ትንቢት

መናገራቸውን ልብ ይሏል። በዚህም ታሪክ ዐፄ ቴዎድሮስና ሁለት ባሕታውያን ትንቢት መናገራቸውና ትንቢቱም መፈጸሙ ተጠቅሷል። ትንቢቶቹም ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው።

## ትንቢቶች

በስንክሳሩ ውስጥ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ አባ ማርቆስና አባ ዘውገ መላእክት ተናገሯቸው የተባሉ ትንቢቶች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

### የዐፄ ቴዎድሮስ ትንቢት

አገሪቱንም አይቶ አንቺ አገር በዘመኑ ሰላም የሚሆን ንጉሥ ከአንቺ ይወጣልና ታላቅ ትባያለሽ ሲል ትንቢት ተናገረላት። .... ቤተ ክርስቲያንም ከተሠራበት ተቀምጦ ከዚህ የእግዚአብሐር ቤት ይሠራል አለ (ቁ.4 : ሚክ. 5፣ 2፡ ማቴ. 2፣ 6)።

### የአባ ማርቆስ ትንቢት

ከንጹሓን መነኮሳት የሆነ አንድ መነከሤም መጣ። በዚህችው የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ግቢ (በተሠራችበት ቦታ) ውስጥ ተቀምጦ "አምላከ ማርቆስ ርዳኝ" እያለ ሌትና ቀን ይጮህ ነበር። መቀመጫውም በከተማው በስተሰሜን ባለችውና አብማ በተባለችው በእመቤታችን በማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለች አንድ ዛፍ ሥር ነበር። ወንጌላዊውን አባት አባ ማርቆስን መጥራት የማያቋርጥ በሆነ ጊዜ ስሙን አባ ማርቆስ አሉት (ቁ. 5)።

ዐፄ ዮሐንስ ራስ አዳልን ወደ ደብረ ታቦር አስጠርተው ካነገሡዋቸው በኋላ ተክለ ሃይማኖት ወልዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ ብለው ሰየሙዋቸው። ለታማኝነት ምልክት ይሆን ዘንድም የቅብጥ ሐዋርያና የእስክንድርያ መንበረ ፓትረያርክ መሥራች ተብሎ የሚታሰበውን የቅዱስ ማርቆስን ፅላት ሰጧቸው። ይህም ፅላት መንቆረር ስለ ተተከለ "አምላከ ማርቆስ እርዳኝ" እያለ ሲጮህ ይውል የነበረው ባሕታዊ ትንቢት ተፈጸመ ተባለ።

የአባ ዘውገ መላእክት ትንቢት ደግሞ ከአባ ማርቆስ የተለየ ነው። አባ ዘውገ፥ አዳል እንደሚነግሡና ታቦተ ማርቆስን ይዘው እንደሚመለሱ በግልጽ ነው የተነበዩት።

### የአባ ዘውገ መላእክት ትንቢት

ይህም ጎልማሳ መንግሥትን ይቀበልና ይለወጥ ዘንድ ወደ ደብረ ታቦር ለመሄድ በተዘጋጀ ጊዜ ስሙ ዘውገ መላእክት ይባል የነበረ የበረሀ መነከሤ የወንጌላዊውን የማርቆስን ሃይማኖት ትሰብክ ዘንድና እንደ ዳዊትና ሰሎሞን ጊዜ ትነግሥ ዘንድ ጊዜው ደርሷልና የምሥራች!! መንግሥትን

ተቀብለህ ስትመለስ የወንጌላዊውን የማርቆስን ታቦት ከአንተ ጋር አምጣው ሲል መልእክት ላከበት (ቁ 10)።

## ተአምራት (ምልክቶች)

ከእምነታውያን ገድላት ውስጥ የርብ መጉደል፣ የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በቀስተ ደመና መሞላትና የቅዱስ ቦታ አፈርና የዮርዳኖስ ጸበል በተአምር መድረስ ይገኙባቸዋል።

### የርብ መጉደል

አንድ ጊዜም ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ወደ አንድ አገር አዘዘው። ሲሄድም ወደ ትልቅ ወንዝ ደረሰ። እጅግም ሞልቶ ነበር። ከወንዙም ሙላት የተነሣ በሐይቁ ውስጥ ቆመ። ሠራዊቱም ሁሉ በደኅና ተሻገሩ። ውሀውም እንደ መጀመሪያው ሙሉ ሆነ። ይህም ነገር እውነተኛና የታመነ ቃል ነው (ቁ. 8)።

ይህ ክስተት በሌሎችም ታሪኮች ተጠቅሷል። ተራው ሕዝብ ግጥም ገጥሞበታል። ሊቃውንቱ ቅኔ ተቀኝተውበታል። ጸሐፊውም ከሌሎች ገለጻዎች አንጻር ሲታይ የተሻለ አምድ ሰጥተውታል። ተክለ ኢየሱስም ይህንን አስመልክቶ፣

ከዚህ በኋላ ደግሞ የራስ ወልደ ሥላሴ ልጅ ደጃች ነጋሽ የሚባል ኃይለኛ በበጌምድር ላይ ተነሳ። ከአምባ ጫራ ገስግሶ በደጃች ይግዛው ላይ አደጋ ጣለና ድል አድርጎ ገደለው። ቀጥሎም ወደ ሰሜን ገስግሶ ራስ ገብረ መድኅንን እንጨት ካብ ላይ ወግቶ ድል አድርጎ አስሮ ወገዳ ወሰደው። ዐፄ ዮሐንስም ልጅህን አምጣ ብሎ ራስ ወልደ ሥላሴን አሰረ። ከዚህ በኋላ ዐፄ ዮሐንስ የራስ አዳልን ጦር አዘዘ። ራስ አዳልም በክረምት በውሀ ሙላት ሄዶ ርብን ተሻግሮ ደጃች ነጋሽን ድል አድርጎ ደጃች ገብረ መድኅንን አስፈትቶ አገሩ ሰሜን መለሰው። ያን ጊዜ ርብ ሞልቶ የነበረው ውሀ ራስ አዳል ሲሻገር ጎደለ። እርሱ ከተሻገረ በኋላ ትኩስ ሙላት ሆነ። ስለዚህ ነገር አዝማሪ እንዲህ አለ።

እንደምናምን እንደ ድሀ
አዳል ከፈለ ውሀ።
ወይ አልሆነ ሙሴ ወይ አልሆነ ኢያሱ
ርብን ከፈለው ከእግር እስከ ራሱ (85)

በማለት ገልጸውታል።

የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ ጸሐፊና የደብረ ማርቆስ አስተዳዳሪ የነበሩት መልአከ ፀሐይ ብሩም ይህንኑ ታምራት አስመልክተው ቀጥሎ የተመለከተውን ሥላሴ ቅኔ ተቀኝተዋል።

ፈጸምከ አዳል ተሰማ መልእክተ ዮሐንስ ሐዋርያ፣
ወእምደለወከ ትቁም ድኅሬሁ በይነ እምትእዛዝ ትጸሙ፣
እስመ ወልድ ርስተ ወላዲ ይነሥእ በአቅሙ፣
ወመልአከ ኃይል ሀብትከ ማኅየዊ ለሕዝበ እስራኤል ኩሎሙ፣

ሰጠቀ ባሕረ ወአንለፎሙ፣
እምዝኒ ጎደገ ለከ ትርጓሜ ስሙ፣
ጸላኢከ ዘሖረ ቀዲሙ (አድማሱ፥ 237)

## ትርጉም

አዳል ተሰማ ሆይ የሐዋርያው የዮሐንስን መልእክት ፈጸምክ፣
በትእዛዝ ከምትደክምም በኋላው መቆምም ትችል ነበር።
ልጅ እንደ አቅሙ የአባቱን ርስት ይወርሳልና።
አዳኝ የሆነው የኀይል መልአክ እድልህም፣
የእስራኤልን ሕዝብ ባሕሩን ሰንጥቆ አሳለፋቸው።
ቀደም ሲል ያለፈው ጠላትህም የስሙን ትርጉም ተወልህ (ትርጉም የራሴ)።

ይህ ቅኔ በርብ ተአምራዊ መጉደል ሠራዊቱ ብቻ ሳይሆን ከታላላቆቹ ሊቃውንት አንዱ የነበሩትና የንጉሡም ታሪክ ጸሓፊ የነበሩት መልአከ ፀሐይ ብሩም ያምኑበት እንደነበር ያሳያል። ምሥጢሩ ሚካኤል የኤርትራን ባሕር ከፍሎ እስራኤልን እንዳሻገራቸው የተክለ ሃይማኖት ዕድልም ርብን ከፍሎ ሠራዊቱን አሻገረው ማለት ነው። ቀደም ሲል ያለፈው ጠላትህ የስሙን ትርጉም ተወልህ ማለትም የወጋሽው ሰው ስም ነጋሽ እንደ ሆነ አንተም ነገሥክ ማለት ነው።

## የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በቀስተ ደመና መሞላት

መልአከ ፀሐይ ተገኘ የዘገቡት ሌላው እምነታዊ ገድል በደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ወረደ ያሉት ቀስተ ደመና ሲሆን፥ እንደሚከተለው ዘግበውታል፣

ከዕለታት አንድ ቀንም በዚህች ቤተ ክርስቲያን ቂሞ ካህናቱ በሦስተኛው መቅደስ እየቀደሱ ሳለ እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ያለ ታላቅ ብርሃን በውስጡ መላ። ንጉሡም ብርሃኑ ከውጭ እንደሆነ ለማየት ወጣ። ከውስጥ ሆኖም አገኘው። በውስጧም ብዙ ተአምር ተደረገ (ቁ.17)።

ይህ ተአምር ለታሪክ ሰዎች ረብ የለውም። ለአማንያን ግን ተአምር ስለሆነ ዐቢይ ነገር ነው። በተክለ ሃይማኖት ቅዱስነት ለሚያምን ጸሓፊ ተአምሩ ያስፈልገዋል። የንጉሡ መንፈሳዊ ገድል ቅድመ እግዚአብሔር ለመድረሱና እግዚአብሔርም በምልክት መልስ ለመስጠቱ ማስረጃው ነውና። ስለዚህ ተአምሩን መጥቀስ አስፈለገ።

## የቅድስት አገር ቅዱስ አፈር (ሕመት) እና ጸበል

በስንክሳሩ ውስጥ የተጠቀሱት ተአምራት ከቅድስት አገር መጡ የተባሉት እምነት (ሕመት) እና ጸበል ናቸው። ይህንኑ አስመልክቶ መልአከ ፀሐይ ተገኘ ቀጥሎ የተመለከተውን ዘግበዋል፥

ከግብጽ አገር የሆነ አንድ ሰውም ነበረ። እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድና ከቅዱሳት ቦታዎች፥ ማለትም ከመካነ ቀራንዮ፥ ከጌታችን ከኢየሱስ

ክርስቶስ መካነ መቃብር ጎልጎታ፥ ከወንጌላዊው ከማርቆስ መካነ መቃብር ከግብጽና ከእስክንድርያ ገዳማት አፈርና ከዮርዳኖስ ውሀ ያመጣለት ዘንድ ንጉሡን ለመነው። እሱም በፈቃዱ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለዳግማዊ ምኒልክ ላከው። ያሰውም ከአንድ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ . . . . ይህንም እያደረገ እያለ ወደ ኢየሩሳሌም የላከው ሰው እንደተመለሰ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከዳግማዊ ምኒልክ ከተማ እንደደረሰና ያለውን ሁሉ እንዳመጣለት የሚነግረው ሰው መጣ። ንጉሡም በአፋጣኝ ላክልኝ የሚል መልእክት ላከ። በዲማ እያለም ላከለት። የቅዱሳት መካናትን አፈርና የዮርዳኖስንም ውሀ ባየ ጊዜ ደስታ ተሰማው። ጸሎቴን ያልከለከለኝ ይቅርታውንም ከእኔ ያላረቀ እግዚአብሔር ይመስገን። አምላኬ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ሲል እግዚአብሔርን አመሰገነው። ከዚህ በኋላ ይህንን ሁሉ እንዲወስዱትና ጎልጎታ ባለው የመቃብር ቦታ እንዲጨምሩት አዘዘ (ቁ. 21)።

ይህንን አስመልክቶ ተክለ ኢየሱስ ቀጥሎ የተመለከተውን ዘግበዋል፥

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በጥር ሊሞት አስቀድሞ በ1892 ዓ. ም. በሰኔ አቡነ ዮሐንስ የሚባል ጳጳስ በአቡነ ሉቃስ ምትክ መጥቶ በጥባት ጎጃም ሊገባ አዲስ አበባ ከርሞ ነበር። ያመጣውም በዐፄ ምኒልክ ፈቃድ ብላታ ገብርኤል የሚባል የግብጽ ሰው ነው። ብላታ ገብርኤል የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወዳጅ ነበር። አቡነ ዮሐንስም ሕፃን ነበርና በፍትወት ታምቶ ከረመ። አፍሮ ወደ አገሩ ተመለሰ። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ቀኖና ሰጠው (110)።

እውነተኛው ታሪክ፥ ተክለ ኢየሱስ እንዳሉት የጳጳስ ጥያቄ ቢመስልም፥ መልአከ ፀሐይ የጳጳሱን ጉዳይ አላወሱም። በሁለት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። አንደኛው ፖለቲካዊ ምክንያት።

ያለ ጳጳስ ንጉሥ ያለ ንጉሥም ጳጳስ ያላሰቡት አፄ ዮሐንስ ከአቡነ አትናቴዎስ ሞት በኋላ ለእሳቸውና ወደ ፊት ሊያነግሡአቸው ላሰቧቸው ሦስት ነገሥታት አራት ጳጳሳት ማስመጣታቸው ይታወቃል። በዚሁ መሰረት፥

ለራሳቸው አቡነ ጴጥሮስን አስቀርተው
ለልጃቸው ለራስ አርአያ አቡነ ማርቆስን
ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አቡነ ሉቃስንና
ለንጉሥ ምኒልክ አቡነ ማቴዎስን

አከፋፍለዋል። ለራስ አርአያ የታሰቡት አቡነ ማርቆስና ራስ አርአያ ሁለቱም ቀደም ሲል አርፈዋል። አቡነ ሉቃስ የጎጃምና ከፋ ንጉሥ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን ለ20 ዓመታት ያህል በደግነት ካገለገሉ በኋላ ታህሳስ 28 ቀን 1892 ዓ. ም. አርፈው አስከሬናቸው ንጉሡ ለራሳቸው በማርቆስ መቅደስ ፊት ለፊት ባሠሩት መካነ መቃብር እንዲያርፍ ተደርጓል (108)።

እንደ ማንኛውም ንጉሥ ሁሉ፥ መንግሥታቸውን ለልጅ ልጅ የሚመኙት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወራሻቸውን ቅብዐ መንግሥት ቀብቶ የሚያነግሥና በብዙ ድካም ያሰሯትን ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚጠብቅላቸው የራሴ የሚሉት ጳጳስ ያስፈልጋቸዋል። ይህንንም ለማድረግ የማዕከላዊው መንግሥት፥ ማለትም የንጉሠ

ነገሥቱ የፀዔ ምኒልክ ፈቃድ ያስፈልጋቸው ኖሯል። በመሆኑም ጥያቄው ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ከተፈቀደ በኋላ ብላታ ገብርኤል የተባሉና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወዳጅ የነበሩ የቅብጥ ሰውና ስማቸው ያልተጠቀሰ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ተልከው አቡነ ዮሐንስ የተባሉ ወጣት ጳጳስ ይዘው መመለሳቸውን ተክለ ኢየሱስ ጠቅሰዋል (110)።

ሆኖም፡ አዲሱ ጳጳስ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ወደ ጎጃም አልተሻገሩም። ምናልባት እንደ ተባለው በፍትወት ታምተው አፍረው ይመለሱ ወይም በሌላ ምክንያት ግልጽ አይደለም። እርግጥ ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ከአንድ በላይ ጳጳስ አናውቅም፣ ቢያንስ በምኒልክ ዘመን። ይህ ሲታይ ፖለቲካዊ ምክንያት ሊገመት ይችላል። የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት፡ በኋላ እንደሚታየው፥ የክልሎች ነገሥታት ታሪክ እንዳይቀጥል ከወሰነና ይህም እንደ ዮሐንስ ከንጉሥ ጋር ከታሰበ የጳጳሱ መምጣት አስፈላጊ አይሆንም። ጉዳዩ እንዲህ ከሆነም መልእክ ፀሐይ ነገሩን ለመጥቀስ አስፈላጊያቸው አይሆንም። ይህ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የጳጳሱን ታሪክ የማይጠቅሱበት ሌላም በቂ ምክንያት አላቸው። ጸሓፊው ዓላማ ያደረጉት የንጉሡን መንፈሳዊ ገድል ለማዘከር እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። እርግጥ አቡነ ዮሐንስ ወደ ሀገረ ስብከታቸው ተሻግረው ቢሆን ኑሮ፥ ተአምሩን የበለጠ ያደምቀው ነበር። ካልሆነ ግን ታሪኩ ለገድሉ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ስለሌለ፥ ስለዚህም መጠቀሱ አስፈላጊ አልሆነም ይሆናል።

## 4. የስንክሳሩ የተለያዩ ባሕርያት

ስንክሳር ትክክለኛውን የሰውና የቦታ ስም፥ እንዲሁም ትክክለኛውን ጊዜ አይጠቅስም።

### 4.1 ዓለማዊ ስም አለመጥቀስ

ለምሳሌ "የዚህ ቅዱስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አባትና እናት የቤተ መንግሥት ተወላጆች ነበሩ። እነሱም በጎጃም ተወለዱ" (እንቀጽ 2)፡፡ የንጉሡ ወላጆች ደጃች ተሰማ ጎሹና ወይዘሮ ምዕላድ መሆናቸው ይታወቃል (66)። ይሁን እንጂ ስንክሳሩ ይህንን አልጠቀሰም። ከሌላ ምንጭ ባናገኘው ከዚህ የታሪክ አጻጻፍ የንጉሡ ወላጆች እነማን እንደነበሩ ለማወቅ አይቻልም ነበር።

"ከንጹሓን መነኮሳት የሆነ አንድ መነኩሴም መጣ" (ቁ.5)፡፡ ይህ መነኩሴ በኋላ አባ ማርቆስ ተባለ ይባል እንጂ ዋናው ስሙ አልታወቀም።

"ይህንንም ልጅ ለጎጃም መስፍን አድርጎ ሾመው" (ቁ.6)፡፡ አዳልን ለማለት ነው። ተክለ ሃይማኖት ከመንገሣቸው በፊት አዳል ይባሉ እንደነበር ከሌላ ምንጭ ባናገኘው ኑሮ የቀድሞ ስማቸውን ለማወቅ እንቸገር ነበር።

"ከአማካሪዎቹ አንዱ" (ቁ.16) የተባሉት ሰው ራስ ወርቄ መሆናቸውን ከሌላ ምንጭ እናውቃለን።

"ከግብጽ አገር የሆነ አንድ ሰውም ነበር" (ቁ. 19)፡፡ የተባሉት ሰው ብላታ ገብርኤል ይባሉ እንደ ነበር ተክለ ኢየሱስ ይነግሩናል ( 110)።

"ያ ሰውም ከአንድ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ጋር" (ቁ.19)፡፡ ኢትዮጵያዊ የተባለው መነኩሴ ማን እንደሆነ አናውቅም።

ቴዎድሮስ፥ ዮሐንስ፥ ተክለ ጊዮርጊስና ራሳቸው ባለታሪኩ ተክለ ሃይማኖትም ከመንገሣቸው በፊት ማን ይባሉ እንደ ነበር አልተወሳም።

4.2. የቦታ ስም አለመጥቀስ

ስንክሳሩ የሰው ስም ብቻ ሳይሆን የቦታ ስምም አይጠቅስም።

"ወደዚሁ ወደ ጎጃሙ መስፍን ከተማም" (ቁ.4)፡፡ መንቆረር ለማለት (87)።
"ወደ አንድ አገር" (ቁ.8)፡፡ አገሩ በጌምድር መሆኑን ተክለ ኢየሱስ (85) ይነግሩናል።

"ወደ ትልቅ ወንዝ" (ቁ.8)፡፡ ርብ ለማለት (85)።

"በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በምኒልክ ከተማም እንደደረሰ" (ቁ.21)። አዲስ አበባ ለማለት (110)።

4.3 ትክክለኛ ጊዜ አለመጥቀስ

በዚህ ቀን ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ቀናተኛ የሆነውና የወንጌላዊው ማርቆስ ልጅ የተባለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አረፈ" (ቁ.1)፡፡ ጥር 3 ቀን፥ 1893 ለማለት።

"እድገቱም ከልጅነቱ ጀምሮ በቤተ እግዚአብሔር ነበር" (ቁ.3)፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ የሚለው ቃል ትክክለኛ ጊዜን አይነግረንም።

ባደገም ጊዜ የአባቶቹ ወንድም ወደሆነው ወደ መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስ ቤት ገባ" (ቁ. 3)፡፡ ባደገም ጊዜ፥ በስንት ዓመቱ?

"መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ በሞቱ ጊዜ ተክለ ጊዮርጊስ ነገሠ። ይህንንም ልጅ ለጎጃም መስፍን አድርጎ ሾመው" (ቁ.6)። በሞቱ ጊዜ የሚለው አሻሚ ነው። 1ኛ ራስ ኃይሉና ቴዎድርስ በዘመን ፈጽሞ አይገናኙም። 2ኛ ዓመተ ምሕረቱን በቀጥታ መጥቀስ ሲቻል እገሌ በሞተ ጊዜ የሚለው አገላለጽ ትክክለኛ ጊዜውን አይነግረንም።

"ከዚህ በኋላ ተክለ ጊዮርጊስ ተሻረ" (ቁ.7)። ከዚህ በኋላ የሚለው ቀኑንና ዓመተ ምሕረቱን በትክክል አይነግረንም።

"እሱንም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሾመው" (ቁ.7)፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚለው ሐረግ በተዘዋዋሪ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በዮሐንስና በአዳል መካከል ስምምነት እንዳልነበር ይገልጻል። ይሁን እንጂ ስምምነቱ ከስንት ጊዜ በኋላ እንደሆነ አያመለክትም።

"አንድ ጊዜም ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ወደ አንድ አገር አዘዘው" (ቁ.2)፡፡ አንድ ጊዜም የሚለው ሐረግ ትክክለኛውን ቀን አይነግረንም።

"ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም ባረፈ ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነገሠ" (ቁ.14)፡፡ ዮሐንስ ያረፉት መቼ ነው?

"ከዕለታት አንድ ቀንም በዚህች ቤተ ክርስቲያን ቆሞ ካህናቱ በሦስተኛው መቅደስ እየቀደሱ ሳለ እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ያለ ታላቅ ብርሃን በውስጡ መላ" (ቁ.17)፡፡ መቼ?

"አቡነ ሉቃስም ከብዙ ጊዜ በኋላ ታኅሳስ 28 ቀን አረፈ" (ቁ. 18)። በ1891 ዓ.ም. ለማለት (108)።

"ከዚህ ነገር በኋላ ንጉሡ ታመመ" (ቁ 20)፡፡ "ከዚህ ቀን ጀምሮ ከዚህ ተነሣ። ወደ ደብረ ወርቅም ሄደ " (ቁ.22) እና የመሳሰሉት ሁሉ መቼ የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳሉ።

ስለዚህ ስንክሳር ትክክለኛ የሰውና የቦታ ስምን ያለመጥቀስና ትክክለኛ ጊዜን ያለማሳየት ባሕርይ ይታይበታል። ምክንያቶቹ ሦስት ይመስሉኛል።

1ኛ የአማርኛ ስሞች፥ ለምሳሌ፥ ተሰማ፥ አዳል፥ ካሳ፥ ጎበዜ፥ በጌምድር፥ ርብ፥ አዲስ አበባ፥ ወዘተ. ለታሪኩ አስፈላጊ ቢሆኑም የአማርኛ ቃላት በግእዙ ምንባብ ውስጥ ቢገቡ ግእዙን ሊበርዙት ይችላሉ። ቋንቋውም (አማርኛ) በዘመኑ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ስላይደለ ከሥነ ጽሑፉ ቋንቋ ጋር መዛበቅ የለበትም በሚል ምክንያት ሊሆን ይችላል።

2ኛ የምሥራቃውያን ሥነ ጽሑፍ ትክክለኛ የቦታ፣ የሰው ስምና ትክክለኛውን ጊዜ የመጥቀስ ባህል የለውም። ይህም በዚሁ ባህል መሠረት የተፈጸመ ይመስላል።

3ኛ ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ፥ አንድ የዚህ ጽሑፍ እንደሚከተለው አስምረውበታል። ቃል በቃል እጠቅሰዋለሁ፤

ወጠናቷ
ቷህህሀፏ

እንደዚህ ባሉ ጽሑፎች ውስጥ 'ምድራዊ' እና 'ተጨባጭ' የሆኑ ሁኔታዎች፥ ስሞችንም ጨምሮ ከጽሑፎቹ ጸታ (genre) አንፃር የሚችሉ ናቸው። እንደዚህ ያሉት መንፈሳውያን ጽሑፎች አንዱ ባለታሪኮችንም ሆነ በእነሱ ዙሪያ የሚሆኑ ድርጊቶችን የማመሳጠር (ı የማድረግ) ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ሊባል የሚችል

እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ካላመሳጠሩ የታሪኩን ጨመቅ (essence) ይስታሉ። ግባቸውንም አይመቱም። አንርሳ! ተክለ ሃይማኖት በአፀደ ሥጋ የነበረ ቢሆንም፥ በጊዜው ወይም ከዚያ በሁዋላ ቅድስናን ስለሚላበስ፥ ስሙን ከሌላው መደባለቁ ወቅቱንም ለይቶ መጥቀሱ ምውታን ከሚሆኑ ተራ ሰዎች በላይ ሊኖረው የሚገባውን ልዕልና ክሡት አድርጎ ዝቅ ማድረግ ይሆናል። ማርያምን መልዕልተ ሰብእ መትሕተ መለኮት አድርጎ ውዳሴዋም ቅዳሴዋም እንደሚመስላት ማለት ነው።

### 4.4. በዘመን የማይገናኙ ታሪኮችን ማገናኘት

ስንክሳሩ በዘመን የማይገናኙ ታሪኮችን በማገናኘት የታሪክና የዘመን መዘበራረቅን ሲያደርግ ይታያል። ለምሳሌ፥ "መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ በሞቱ ጊዜ" (ቁ.4)፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች በዘመን አይገናኙም። ኃይለ ኢየሱስ የታላቁ ራስ ኃይሉ ስም እንደሆነ ይታወቃል። ታላቁ ራስ ኃይሉ ሰኔ 30 ቀን 1787 ማረፋቸውን እናውቃለን (Blundel 1922:163)። ስለዚህ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ከሞቱት ከቴዎድሮስ ጋር የ73 ዓመታት የዘመን ልዩነት እያለ "መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ በሞቱ ጊዜ" ማለቱ ታሪኩን የተምታታና የተሳሳተ ያደርገዋል (ስንክሳሩ ኃይለ ኢየሱስ የሚላቸው ደጃች ተድላን ካልሆነ በቀር)።

### 4.5. የዝምድና አቆጣጠር ስሕተት

ስንክሳሩ የዝምድና አቆጣጠር ስሕተትም ይታይበታል። "የአባቶቹ ወንድም ወደ ሆነው ወደ መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስ ቤት ገባ" (ቁ.3)። የአባቶቹ ወንድም የተባሉ ታላቅ ራስ ኃይሉ ከሆኑ ስሕተት ነው[5]። ኃይለ ኢየሱስ፥ ማለትም ታላቁ ራስ ኃይሉ፥ ለተክለ ሃይማኖት በቀጥታ መሥመር የሚገኙ ምንጅላት እንጅ የአባታቸው ወንድም አይደሉም። ግንኙነቱም ዝምድና ሳይሆን አባትነትና ልጅነት ነው። አቆጣጠሩም አዳል (ተክለ ሃይማኖት)፥ ተሰማ፥ ጎሹ፥ ድንቅነሽ፥ ኃይለ ኢየሱስ ነው (49-52፥ 66)።

### 4.6. ለዓለማዊ ታሪኮች ትኩረት አለመስጠት

ስንክሳር እራሱን ከቅዱሳት መጻሕፍት ይመድባል። ስለዚህ፥ ታሪኩም ወደ ቅዱሳት ተግባራት ያመዝናል። በዚህ ምክንያት ለተክለ ሃይማኖት ዓለማዊ ታሪክ ትኩረት አልተሰጠውም።

## 5. የስንክሳሩ ዋና ጭብጥ (ይዘት)

ከፍ ብሎ የተዘረዘረው ሐሳብ ሲጨመቅ ቀጥሎ የተመለከተው አንድምታ (ትርጉም) ይኖረዋል። ተክለ ሃይማኖት ቀድሞውንም አገር የመምራትና የማስተዳደር

---

[5] የደጃች ተድላ የክርስትና ስም ኃይለ ኢየሱስ ከሆነ ብቻ ስንክሳሩ ትክክል ይሆናል።

ልምድ ያላቸው ነገሥታት ዘር፡ አስተዳደጉም የሕገ እግዚአብሔር ትምህርት ከሚሰጥበት ከቤተ ክህነት ትምህርት ቤት በመሆኑ፡ ንጉሥነቱ አግባብ ነው። ይሁንና የነገሠው አገር የመምራትና የማስተዳደር ልምድ ካላቸው ቤተ ሰቦች በመወለዱና ሕገ እግዚአብሔርን በመማሩ ብቻ አይደለም፡ በእግዚአብሔር ስለተመረጠም ጭምር እንጂ። ይህንንም አስቀድመው ከተነገሩት ትንቢቶችና ከተፈጸሙት ምልክቶች መረዳት ይቻላል። ተክለ ሃይማኖት ሥዩመ እግዚአብሔር ለማለት። (የታሪክ ሰዎች ይህንን ከተክለ ሃይማኖት ይልቅ ለአልጋው እኛ እንቀርበው ነበር ለሚሉት የተሰጠ መልስ ሊሉት ይችላሉ።)

መንቀረር አዲሷ ቤተ ልሔም ናት። ትንቢት ተነግሮላት ሱባዔ ተቆጥሮላት እንጂ በዘፈቀደ ታላቅ አልሆነችም። (የታሪክ ሰዎች ፀረ መንቀረር አቋም ላላቸው የተሰጠ መልስ ሊሉት ይችላሉ)። ይህም ይታወቅ ዘንድ፥ በመጀመሪያ ዐፄ ቴዎድሮስ ትንቢት ተናግረውላታል። የመንቀረር ታላላቅ ሰዎችም ትንቢቱን በጆሮአቸው ሰምተዋል። ስለዚህ የመንቀረር ታላቅነትና የአዳል ንጉሥነት እንደ ዐፄ ተዎድሮስ፥ እንደ አባ ማርቆስና እንደ ባሕታዊ ዘውገ መላእክት ባሉ፥ ሀብተ ትንቢት በተሰጣቸው ታላላቅ ሰዎች ትንቢት ተረጋግጧል። (ነገር ሁሉ በምርጫና በእድል እንጂ በግል ጥረት ብቻ አይደለም።)

ነገሥታት (ለምሳሌ ዐፄ ቴዎድሮስ) መነኮሳት (ለምሳሌ አባ ማርቆስና ባሕታዊ ዘውገ መላእክት) ኀላፍያቱንና መጻእያቱን ሊተነብዩ ይችላሉ።

በስንክሳር የተዘገበው የተክለ ሃይማኖት ታሪክ በገሀዱ ዓለም የተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ እንጂ ልብ ወለድ አይደለም። መስፍንነቱን ከእውኑ ንጉሠ ነገሥት ተክለ ጊዮርጊስ፥ ንጉሥነቱን ከእውኑ ንጉሠ ነገሥት፥ ከዮሐንስ፡ ከምኒልክ ታሪክ መርምሩና ዕወቁ። የተክለ ሃይማኖት "ንጉሠ ከፋ ወጎጃም" መሆን በደራሲው ወይም በጎጃም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም (ኢትዮጵያ) የታወቀና የተረጋገጠ፥ እውነተኛና የታመነ መሆኑን መርምሩና ዕወቁ። (የተክለ ሃይማኖት መንግሥ እውነት እንጂ ድርሰት አይደለም።)

ተክለ ሃይማኖት ለመንጋው የሚራራ ቸር እረኛ፥ ጻድቅና እግዚአብሔርን... የሚፈራ በመሆኑ ለቅዱስነት በቅቷል። ይሄውም ይታወቅ ዘንድ፥ ር... ታዝዞለታል (ቁ.8)። ቀስተ ደመና ከሰማይ ወርዶለታል (ቁ.17)። ከፀአ... ነፍሱ ጥቂት ቀደም ብሎ ለሥርዐተ ቀብሩ ዝግጅት የሚሆን አፈርና ጸበ... በወቅቱ በተአምር ከኢየሩሳሌም ደርሶለታል (ቁ.23)። (በስሙ ቤ... ክርስቲያን ይታነጽለት፡ ፅላት ይቀረጽለት።)

ንጉሡ፡ ስሙ እንደሚያመለክተው፥ በእውነት ተክለ ሃይማኖት ርቱዐ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ነው። በእውነት የወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ ልጅ ነው። ስለዚህ "ቅዱስ" መባሉ ተገቢ ነው።

ለዚህ አባባል ቀጥሎ የተመለከተው ታሪክ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል።

እንደሚታወቀው፥ ዐፄ ዮሐንስ፥ ማርቆስ አባታችን፣ እስክንድርያ እናታችን፣ ሃይማኖታችን ሁለት ልደት ባይ ናቸው። ራስ አዳልም የዚህ ባህል አራማጅ በመሆናቸው በሃይማኖት ረገድ ለዐፄ ዮሐንስ አጋር ናቸው። ንጉሠ ነገሥቱም ይህንኑ በመመኘት ነው "ተክለ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ወልዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ" የሚል የቅጽል ስም የሰጧቸው። የማርቆስንም ጽላት ለምስክርነት ሰጥተው ይህንኑ ባህል በግዛታቸው እንዲያስፋፉ አደራ አሏቸው። እርሳቸውም በተሰጣቸው አደራ መሠረት ከዚህ ባህል ሌላ የሚከተሉትን ሰዎች እየተከታተሉ በጥብቅ ይቀጡና ያጠፉ እንደነበር የሚናገሩ ሽማግሌዎች አሉ (ሊቀ ጠበብት መቆያ፣ የደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበሩ)። አለቃ አጥሜ ይህንኑ በተመለከተ "ራስ አዳልም ጎጃም ተሻገሩ። ቅባት የተባለውንም ሲያጠፉ እስላሙን ሲያቀርቡ . . ." (51) በማለት ይጽፋሉ።

ተክለ ኢየሱስ፥ በበኩላቸው፥ "መምህር ወልደ ጊዮርጊስን አፈ ጉባኤ አድርጎ፥ ቅብዐት ሃይማኖት ይጥፋ ብሎ በተዋሕዶ ሃይማኖት አንገባም ያሉትን ሰዎች እየገረፈ አሠራቸው" በማለት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለሁለት ልደት ባህል ተቆርቋሪ እንደነበሩ ይመሰክራሉ። የዚህ ስንክሳር ጸሓፊ እንደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የሁለት ልደት ባህል ደጋፊና ተቆርቋሪ ናቸው። ስለሆኑም ይህች ማርቆስ የሰበካት ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ርትዕት (የቀናች) ናት። ቅድስት ናት። የዚህች ሃይማኖት ሐዋርያና ሰባኪ የሆነው ተክለ ሃይማኖትም ሃይማኖቱ ቅድስት እንደሆነች እሱም ቅዱስ ነው። አባቱ ማርቆስ ሰባኬ ወንጌልና ቅዱስ እንደሆነ ተክለ ሃይማኖትም ሰባኬ ወንጌልና ቅዱስ ነው። የወንጌላዊውና የሰባኬ ወንጌሉ ቅዱስ ማርቆስ መንበር እስክንድርያ እንድትባል የአዲሱ ሰባኬ ወንጌል የቅዱስ ተክለ ሃይማኖትም መንበር የሆነችው መልዕልተ አድባራት ደብረ ፀሐይ ማርቆስ አዲሷ እስክንድርያ ናት።

ለተክለ ሃይማኖት ቅዱስነት መሠረቱ አስቀድሞ ከእናቱ ማሕፀን በእግዚአብሔር መመረጡ ነው። ይህም ገና ከመንገሡ በፊት ስለ እሱ ትንቢት በመነገሩ ይታወቃል። ሆኖም፥ ለቅዱስነቱ ማረጋገጫው ስለእሱ የተነገሩት ትንቢቶች ብቻ አይደሉም፣ በእሱ ባደረው የእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት የተከናወኑ መንፈሳዊ ሥራዎቹም ጭምር እንጂ። በእግዚአብሐር የተመረጠው ተክለ ሃይማኖት የጎጃምና የሌሎችም የምዕራብ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት፥ በተለይም የመልዕልተ አድባራት ደብረ ፀሐይ የበለጠ እንዲስፋፉ፥ እንዲታነጹና ለመንፈሳዊ አስተዳደራቸው የሚያስፈልጋቸውን መዋዕለ ንዋይ እንዲያገኙ አድርጓል። በከፋና በሌሎቹም ክርስትና ባልተስፋፋባቸው ግዛቶቹ ክርስትናን በማስፋፋት ሐዋርያዊ ተልእኮ ፈጽሟል። ስለዚህ፥ ቀደም ሲል ስለእሱ የተነገሩት ትንቢቶችና የተፈጸሙለት ተአምራት ከፈጸማቸው ተግባራት ጋር ተዳምረው ቅዱስነቱን ያረጋግጣሉ።

## ማጠቃለያ


ከፍ ሲል እንደተመለከትነው፥ የስንክሳሩ የአጻጻፍ ስልትና ይዘት ሲጠቃለል የሚከተለው አንድምታ (ትርጉም) ይኖረዋል።

በመጀመሪያ፥ ከቅድስና ጋር የተየያዙ መንፈሳዊ ገድላትን ዓላማ አድርጓል። ለምሳሌ፥ የአብያተ ክርስቲያናት ግንባታን፣ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚደረግ ስጦታንና የዚሁ ቅድስና መልስ የሆኑ ትንቢቶችንና ምልክቶችን ትኩረት ሰጥቶ ዘግቧል። በተቃራኒው፥ ከመንፈሳዊው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ዓለማውያን ገድላት፥ እንደ ጦርነቶችና አገር እንደማቅናት እንቅስቃሴዎች፣ ድንበርንና ግዛትን የማስከበር ፍልሚያዎች በአብዛኛው አልተጠቀሱም፤ ዓለማዊ ጉዳዮች በመሆናቸው። ለምሳሌ፥ በሥልጣን ሽኩቻ ከአጎታቸው ከራስ ደስታ ተድላ ጋር ያደረጓቸው ሁለት ጦርነቶች (80)፣ በምዕራብ ደቡብ የተደረጉ አገር የማቅናት እንቅስቃሴዎች (84፣ 94)፣ ከምኒልክ ጋር በግዛት ጥያቄ መነሻ የተደረገው የእምባቦ ጦርነት (88-89) እና በጌምድር ውስጥ ከነራስ ወልደ ማርያም ጋር የተደረጉ ጦርነቶች (84) አልተወሱም። የዐድዋ ጦርነትም (101) ሆነ ከደርቡሽ ጋር የተደረጉት ሁለት የታወቁ ታላላቅ ጦርነቶች፥ ምንም እንኳን በሃይማኖት በማይመሳሰሉ ሁለት ወገኖች መካከል የተደረጉ ቢሆንም፥ (ተክለ ጻድቅ 1936፣93)፥ በስንክሳሩ አልተወሱም። ጸሓፊው በታሪካቸው እንደተወሳው፥ በሚናገሩትም ሆነ በሚጽፉት ጠንቃቃ ስለሆኑ ጦርነቶቹ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ መነሻ የሌላቸው መሆኑን በመረዳት ትተዋቸው ይሆናል። ወይም፥ በእሳቸው እምነት፥ እዚያ የታዩ ምልክቶች የሉም። እርግጥ ጦርነት የተጠቀሰበት አጋጣሚም አለ። ለምሳሌ፥ በጌምድር ውስጥ ራስ አዳል ከራስ ወልደ ሥላሴ ልጅ ከደጃች ነጋሽ ጋር ያደረጉት ጦርነት (85) በስንክሳሩ ተጠቅሷል። የተጠቀሰበት ምክንያት ግን በክረምት ምክንያት ሞልቶ የነበረው ርብ የተባለው ወንዝ ራስ አዳል ሲሻገሩ በመጉደሉና ይህም እንደ ታላቅ ተአምር በመቆጠሩ ነበር። በጸሓፊው እምነት በተአምር የታጀቡ እንደዚህ ዐይነት ክስተቶች ሲያጋጥሙ ዓለማውያንም ቢሆኑ ይዘገባሉ። ተአምር ነውና።

በመሠረቱ፥ በስንክሳር፥ ቅድስና ሊረጋገጥ የሚችለው ከሰማይ በሚሰጡ ምልክቶች እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ነው በርካታ ተአምራት በቁ. 4፥ 5፥ 8፥ 10፥ 11፥ 17፥ 21፥ 24 በአጽንዖት የተወሱት። የቀሩትም ቁጥሮች ቢሆኑ የእነዚህ ተአምራት መንደርደሪያዎች ናቸው።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፥ የስንክሳሩን ይዘት ቀጥሎ የተመለከተው ስእል ይገልጸው ይሆናል።

ስለዚህ ስንክሳሩ በመሠረቱ መንፈሳውያን ገድላትን፥ ተአምራትን፥ ትንቢታትንና ምልክቶችን ዓላማ አድርጓል። ሆኖም ግን፥ ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተጨባጭና ተዳሳሽ የሆኑ ዓለማውያን ድርጊቶችንም በመጠኑ ማስተላለፉን እንገነዘባለን።


ስለ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተጻፈው ስንክሳር ይዘት
ታሪክ
ገድል
ተክለ ሃይማኖት ንጉሥ ነው፡፡
ተክለ ሃይማኖት ቅዱስ ነው፡፡
ታሪኩን አንብበው ይረዱ
ተአምራቱን ሰምተው ይመኑ

## ዋቢ መጻህፍት

"የብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ስንክሳር ጥር 3 ቀን"። ያልታተመ።

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ። 1981። "የቤተ ክርስቲያን የአማርኛ መዝገበ ቃላት"። ቅፅ 2። ሃይደልበርግ፤ ያልታተመ።

ተክለ ኢየሱስ ። "የኢትዮጵያ ታሪክ።" ያልታተመ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። 1936። *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ።* አዲስ አበባ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

_ _ _ _ _ _ ። 1982። *አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት።* አዲስ አበባ፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አጥሜ (አለቃ አፅመ ጊዮርጊስ)። "የጋላ ታሪክ" (ያልታተመ)። የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም።

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)። 1963። *መጽሐፈ ቅኔ።* አዲስ አበባ፥ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ገብረ ሥላሴ (ጸሐፌ ትእዛዝ)። 1959። *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ።* አዲስ አበባ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

Bizuayehu,Birhanu, 1971. "Adal Abba Tanna. Nigus of Gojjam and Kaffa 1850-1901." A paper presented in partial fulfillment of the Degree of Bachelor of Arts, submitted to the Department of History, Addis Ababa University.

Blundel, Weld. 1922. *The Royal Chronicles of Abyssinia.* Cambridge: Cambridge University Press.

Budge, E. A. 1928. *The Book of the Saints of the Ethiopian Church: A Translation of the Ethiopic Synaxarium. መጽሐፈ ስንክሳር.* Cambridge: Cambridge University Press.

Duesing. H. 1990. *Liefert das aethiopische Synaxar Materialien zur Geschichte Abessniens*. Goettingen.

Guidi, Ignazio. *Annales regium Iyasu II et Iyo'as.* CSCO.

Hofer, J. and K. Rahner Synaxar. 1986. in '*LThK*' IX. pp.1224-1225 Freiburg im Breisgau. Herder.

# አባሪ ርእስ

ግእዝ

1 ወበዛቲ ዕለት አዕረፈ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ንጉሠ ከፋ ዘተሰምየ ርቱዐ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ወልዱ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ።

2 ወለዝንቱ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ኮኑ አቡሁ ወእሙ እምአዝማደ ቤተ መንግሥት ወተወልዱ በብሔረ ጎጃም።

3 ወእምንእሱ ኮነ ህይወቱ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር። ወሶበ ልህቀ ቦአ ውስተ ቤተ መስፍን ኃይለ ኢየሱስ ዘውእቱ እምአኃወ አበዊሁ።

4 ወበውእቱ መዋዕል በጽሐ ብሔረ ጎጃም ቴዎድሮስ ንጉሠ ኢትዮጵያ ወቦአ ኀበ ትዕይንተ ውእቱ መስፍን ዘብሔረ ጎጃም ወርእያ ለሀገር ወተነበየ ላዕሌሃ ወይቤ አንቲኒ ሀገር ትከውኒ ልዕልተ እስመ እምኔኪ ይወጽእ ንጉሥ ዘይከውን ሰላም በመዋዕሊሁ። ወሶበ ይቤ ዘንተ ቀርቡ እደው እምአዕሩገ ይእቲ ሀገር ወሰምዕዎ። ወነበረ ውስተ መካን ኀበ ተሐንጸት ቤተ ክርስቲያኑ ለማርቆስ ወይቤ ዝየ ይትሐነጽ ቤተ ክርስቲያኑ ለእግዚአብሔር።

5 ወመጽአ ፩ መነኮስ እመነኮሳት ንጹሓን ወኮነ ይጸርህ መዐልተ ወሌሊተ ውስተ ይእቲ መካን ዘተሰምየት ደብረ ማርቆስ እንዘ ይብል አምላከ ማርቆስ ርድእኒ። ወንብረቱሰ ኮነ ታህተ አሐቲ ዖም በቤተ ክርስቲያን ዘእግዝእትነ ማርያም ዘሀለወት በሰሜነ ትዕይንት ዘተሰመይ አብማ። ወኢያበውህ መነኒ ይቅረብ ኀቤሁ ዘእንበለ ውእቱ ወልድ ተክለ ሃይማኖት። ወሶበ ኮነ ዘኢየአርፍ እምተዘክሮተ አብ ማርቆስ ወንጌላዊ ሰመይዎ ስሞ አባ ማርቆስ።

6 ወእምድኅረ ሞቱ ኃይለ ኢየሱስ መስፍን ወቴዎድሮስ ንጉሠ ኢትዮጵያ ነግሠ ተክለ ጊዮርጊስ ወሤሞ ለውእቱ ወልድ መስፍነ ለብሔረ ጎጃም።

7 ወእምዝ ተስዕረ ተክለ ጊዮርጊስ ወነግሠ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ወሤሞ ለውእቱ እምድኅረ ኅዳጥ መዋዕል። ወአፍቀሮ ወኮነ ሎቱ ከመ ወልዱ። ወኮነ ጻድቀ ወኄረ ወፈራሄ እግዚአብሔር።

ትርጉም

1 በዚህ ቀን ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ቀናተኛ የሆነውና የወንጌላዊው ማርቆስ ልጅ የተባለው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አረፈ።

2 የዚህ ቅዱስ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አባትና እናት የቤተ መንግሥት ተወላጆች ነበሩ። እነሱም በጎጃም ተወለዱ።

3 እድገቱም ከልጅነቱ ጀምሮ በቤተ እግዚአብሔር ነበር። ባደገም ጊዜ የአባቶቹ ወንድም ወደ ሆነው ወደ መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስ ቤት ገባ።

4 በዚህም ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ ወደ ጎጃም መጣ። ወደዚሁ ወደ ጎጃሙ መስፍን ከተማም ገባ። አገሪቱንም አይቶ አንች አገር በዘመኑ ሰላም የሚሆን ንጉሥ ከአንች ይወጣልና ታላቅ ትባያለሽ ሲል ትንቢት ተናገረላት። ይህንንም ባለ ጊዜ ከዚህች አገር ሽማግሌዎች ቀርበው ሰሙት። ቤተ ክርስቲያንም ከተሰራበት ተቀምጦ ከዚህ የእግዚአብሔር ቤት ይሰራል አለ።

5 ከንጹሓን መነኮሳት የሆነ አንድ መነኩሴም መጣ። በዚህችው ደብረ ማርቆስ በተባለችው ቤተ ክርስቲያን (በተሰራችበት ቦታ) ውስጥ ተቀምጦ አምላከ ማርቆስ ርዳኝ እያለ ሌትና ቀን ይጮህ ነበር። መቀመጫውም በከተማው በስተሰሜን ባለችውና አብማ በተባለችው በእመቤታችን በማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለች አንድ ዛፍ ስር ነበር። ወንጌላዊውን አባት አባ ማርቆስን መጥራት የማያቋርጥ በሆነ ጊዜ ስሙን አባ ማርቆስ አሉት።

6 መስፍኑ ኃይለ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ በሞቱ ጊዜ ተክለ ጊዮርጊስ ነገሠ። ይህንንም ልጅ ለጎጃም መስፍን አድርጎ ሾመው።

7 ከዚህ በኋላ ተክለ ጊዮርጊስ ተሻረ። የኢትጵያ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስም ነገሠ። እሱንም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሾመው። ወደደውም። እንደ ልጅም ሆነው። ጻድቅና ቸር እግዚአብሔርንም የሚፈራ ሆነ።

8 ወበ፩ መዋዕል አዘዞ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ኀበ ፩ ብሔር ወሖረ። ወእንዘ የሐውር በጽሐ ኀበ ፈለግ ዐቢይ ወምሉእ ጥቀ። ወእምልዐ ውእቱ ፈለግ ቆመ ውስተ ሐይቅ ወኀዘነ ብዙኀ እስመ ውእቱ ኄር ኖላዊ። ወቆመ ውእቱ ማይ ላዕለ ወታህተ ወአደዉ ኵሉ ሠራዊቱ በሰላም ወበዳህና። ወኮነ ማይ ከመ ቀዲሙ ምሉእ። ወዝ ነገር ቃለ ጽድቅ ወእሙን ውእቱ። ወእምዝ ፈጺመ መልእክቶ ወአተወ ብሔሮ።

9 ወሶበ ርእየ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ከመ ይፈጽም ትእዛዞ ወፈድፋደ ይገብር ስምረቶ ጸውዖ እንዘ ሀሎ ደብረ ታቦር ከመ ያንግሦ።

10 ወሶበ ተደለወ ውእቱ ወረዛ ለሐዊር ኀበ ደብረ ታቦር ከመ ይንሣእ ሎቱ መንግሥቶ ወይሰወጥ ፈነወ ሎቱ መነኮሰ ዘውስተ ጾማዕት ዘውእቱ ስሙ ዘውገ መላእክት። ወይቤሎ ብስራትከ እስመ በጽሐ ጊዜሁ ከመ ትስብክ ሃይማኖቶ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ወትነግሥ ከመ መዋዕለ ዳዊት ወሰሎሞን። ወእምከመ ነሣእከ መንግሥተ ወተመየጥከ አምጽኦ ምስሌከ ለታቦተ ማርቆስ ወንጌላዊ።

11 ወእምድኅረ ሰምአ ዘንተ መልእክተ ሖረ ኀበ ደብረ ታቦር። ወአንገሦ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን በብሔረ ከፋ ወብሔረ ጎጃም ወበካልኣን አሕጉር እምብሔረ አረማውያን። ወሰመየ ስሞ ተክለ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ወልዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ። ወሶበ ሰመዮ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን በዝንቱ ስም ተዘከረ ቃሎ ለውእቱ መነኮስ ዘፈነወ ሎቱ ውእተ መልእክተ። ወዝ ስሙ ኮነ እውቀ ወክሡተ በኵሎሙ በሐውርት ወመዓዶ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ወይቤሎ ወልድየ ፅናዕ በሃይማኖት ወከመዝ መሀር ወገሥጽ ወንሣእ ምስሌከ ታቦተ ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ይኩን ስምአ ለሃይማኖት።

12 ወነሥአ ታቦተ ማርቆስ ወንጌላዊ ወሐነጸ ቤተ ክርስቲያን ሠናይተ ወገብረ ላቲ ሠላሰ ሕዋራተ በአምሳለ መቅደስ ዘገብረ መቃርዮስ እስክንድርያዊ በማዕከለ ሮምያ ወቀኀስጥንጥንያ ዘባቲ ገብረ ማርቆስ ብዙኀተ ተአምራተ። ዘየማንሂ ሰመየ መቅደሰ ማርቆስ አቡነ ወንጌላዊ። ወዘማዕከልሰ በስመ ሥሉስ ቅዱስ አምላክነ። ወዘፀጋምሂ በስመ ቅድስት ድንግል ማርያም እግዝእትነ።

13 ወአመ መድቅሓ ለይእቲ መቅደስ ገብረ ውስቴታ መቃብረ ዘባቲ ክልኤ ክፍል በአንጻረ መቅደሱ ለማርቆስ ወንጌላዊ። ወሰመያ ለይእቲ መካነ ጎልጎታ ዘንጉሥ። ወለቤተ ክርስቲያንሂ ሰመያ ደብረ ፀሐይ ዳግሚት እስክንድርያ። ወለትዕይንቱ ደብረ ማርቆስ።

8 አንድ ጊዜም ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ወደ አንድ አገር አዘዘው። ሲሄድም ወደ ትልቅ ወንዝ ደረሰ። እጅግም ሞልቶ ነበር። ከወንዙም ሙላት የተነሳ በሐይቁ ውስጥ ቆመ። ሠራዊቱም ሁሉ በደህና ተሻገሩ። ውሃውም እንደ መጀመሪያው ሙሉ ሆነ። ይህም ነገር እውነተኛና የታመነ ቃል ሆነ። ከዚህ በኋላ ተልእኮውን ፈጸመ ወደ አገሩም ተመለሰ።

9 ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም ፈቃዱን እንዲፈጽም ፈቃዱንም አብልጦ እንዲያደርግ በተመለከተ ጊዜ ያነግሠው ዘንድ ወደ ደብረ ታቦር ጠራው።

10 ይህም ጎልማሳ መንግሥትን ይቀበልና ወደ ዐፄ ዮሐንስ ይገባ ዘንድ ወደ ደብረ ታቦር ለመሄድ በተዘጋጀ ጊዜ ስሙ ዘውገ መላእክት ይባል የነበረ የበረሃ መነኩሴ የወንጌላዊውን የማርቆስን ሃይማኖት ትሰብክ ዘንድና እንደ ዳዊትና ሰሎሞን ጊዜ ትነግሥ ዘንድ ጊዜው ደርሷልና የምሥራች። መንግሥትን ተቀብለህ ስትመለስ የወንጌላዊውን የማርቆስን ታቦት ከአንተ ጋር አምጣው ሲል መልእክት ላከበት።

11 ይህንንም መልእክት ከሰማ በኋላ ወደ ደብረ ታቦር ሄደ። ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም በከፋ፥ በጎጃምና በሌሎችም ኢአማናውያን አገሮች አነገሠው። ስሙንም ተክለ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ወልዱ ለማርቆስ ወንጌላዊ አለው። ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም በዚህ ስም ሰጠራው ያንን መልእክት የላከበትን መነኩሴ ቃል አሰበ ። ይህም ስሙ በአገሮች ሁሉ የታወቀና የተገለጠ ሆነ። ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም ወደደው። አለውም ልጄ በሃይማኖት ጽና እንዲህም አስተምር ገሥጽ። ለሃይማኖትም ምስክር ይሆን ዘንድ የወንጌላዊውን የማርቆስን ታቦት ከአንተ ጋር ውሰድ።

12 የወንጌላዊውን የማርቆስን ታቦትም ወሰደ። ያማረች ቤተ ክርስቲያንን ሠራ። እስክንድርያዊው መቃርዮስ በሮምና በቁስጥንጥንያ መካከል ባሠራትና ወንጌላዊው ማርቆስ ብዙ ተአምራት ባደረገባት ቤተ ክርስቲያን አምሳል ሦስት መቅደሶችን አደረገላት። የቀኙን የአባታችን የወንጌላዊው የማርቆስ መቅደስ አለው። መካከለኛውን በአምላካችን በሥሉስ ቅዱስ ስም ሰየመው። የግራውን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ሰየመው።

13 ይህችንም መቅደስ በሠራት ጊዜ በወንጌላዊው በማርቆስ መቅደስ ፊት ለፊት ሁለት ክፍል ያላትን መቃብር አደረገ። ይህችንም ቦታ የንጉሥ ጎልጎታ አላት። ቤተ ክርስቲያኗንም ደብረ ፀሐይ ዳግሚት እስክንድርያ ከተማዋንም ደብረ ማርቆስ አላት።

14 ወሶበ አእረፈ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ነግሠ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ወውእቱ ኃያል ወመስተአግስ ዘኢያመጽእ መንሱተ ከሎ አሚረ ወአፍቀሮ ብዙኀ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወአንገሦ ዳግመ ወወሀቦ አክሊለ መንግሥት፡፡

15 ወንጉሥኒ ተክለ ሃይማኖት ሐነጸ ብዙኃተ አብያተ ክርስቲያናት በብሔረ አረማውያን ወብሔረ ክርስቲያን። ወለአድባራትኒ ብሔረ መንግሥቱ አልቦ ዘኢገብረ ሠናያተ ወፈድፋደሰ ለደብረ ማርቆስ። ወወሀቦ ብዙኃነ ጉልታተ።

16 ወሶበ አፈድፈደ ውሂበ ብዙኃት አህጉር ይቤሎ ፩ እመማክርቲሁ ለምንት ታበዝኅ ዘኢይከውን ወኢይጸንእ እምድኅሬከ ወይቤሎ አንሰ እሁብ ለቤተ ክርስቲያን ጊዜ እብሬትየ ወአኀድግ ለቤተ ክርስቲያን ዘይከውነኒ ለረብሐ መንግሥትየ ወለእመኒ ኢጸንዐ ድኅረ ህልፈትየ። ኢየኃጉል እግዚአብሔረ አስብየ ዘገበርኩ በህይወትየ።

17 ወበአሐቲ እለት እንዘ ይቄድሱ ካህናት ውስተ ሠላስ መቅደስ መልአ ብርሃን አቢይ ውስቴቱ ከመ ቀስተ ደመና ዘክረምት። ወወጽአ ንጉሥ ለእመ ይከውን ዝንቱ ብርሃን እምአፍአ ወረከቦ እምውስጥ። ወተገብረ ብዙኀ ተአምር በውስቴቱ።

18 ወቦ ምስሌሁ ጳጳስ ዘስሙ ሉቃስ። ወእምድኅረ ብዙኅ መዋዕል አእረፈ አቡነ ሉቃስ አመ፳ወ፰ ለታህሳስ ወተቀብረ በአሐቲ ክፍል እምይእቲ መካን ቅድስት።

19 ወነበረ ፩ ብእሲ ዘእምብሔረ ግብጽ ወሰ አሎ ለንጉሥ ይንግድ ኢየሩሳሌም ወያምጽእ ሎቱ መሬተ እመካናት ቅዱሳት ዘውእቶሙ ቀራንዮ መካነ መስቀል ወጎልጎታ መካነ መቃብሪሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወእምገዳማተ ግብጽኒ ወእስክንድርያ መካነ መቃብሪሁ ለማርቆስ ወንጌላዊ ወማየ ዮርዳኖስ። ወፈነዎ በፈቃዱ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ወሖረ ውእቱ ብእሲ ምስለ ፩ መነኮስ ኢትዮጵያዊ ውስተ ኢየሩሳሌም።

20 ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ሐመ ንጉሥ። ወጸውዐ ካህናተ እለ ቤተ ክርስቲያን ይጸልዩ ላዕሌሁ ወይቅብእዎ ቅብዐ ጸሎት በስሙ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ወኮነ ይጼልዩ ሎቱ ካህናት ወይመጥውዎ ቁርባነ።
ወእምዝ አዘዘ ከመ ይሰድዎ ለዝንቱ ኰሉ ወይደይዎ በመካነ መቃብሪሁ ዘሰመየ ጎልጎታ።

14 ንጉሠ ጽዮን ዮሐንስም ባረፈ ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነገሠ። እሰ -ም ኃያልና ታጋሽ ሁልጊዜም ጥፋትን የማያመጣ ነበር። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትንም እጅግ ወደደው። እንደገናም አነገሠው። የመንግሥት ዘውድንም ሰጠው።

15 ንጉሡ ተክለ ሃይማኖትም በኢአማናውያውና በክርስቲያን አገሮች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ሠራ። በመንግሥቱም ውስጥ ላሉት አድባራት ያላደረገው በጎ ነገር የለም። ይልቁንም ለደብረ ማርቆስ ያላደረገው ነገር የለም። ብዙ ጉልቶችንም ሰጠው።

16 ብዙ አገሮችንም መስጠት ባበዛ ጊዜ ከአማካሪዎቹ አንዱ ከአንተ በኋላ የማይሆነውንና የማይጸናውን ለምን ታበዛለህ? አለው። እሱም እኔ በዘመኔ ለቤተ ክርስቲያን እሰጣለሁ ለመንግሥቴ ጥቅም የሚሆነውንም ለቤተክርስቲያን እተዋለሁ። ካለፍኩ በኋላ ባይጸና ግን በህይወቴ ያደርግሁትን እግዚአብሔር ዋጋየን አያጠፋም አለው።

17 ከእለታት አንድ ቀንም በዚህች ቤተ ክርስቲያን ቆሞ ካህናቱ በሦስተኛው መቅደስ እየቀደሱ ሳለ እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ያለ ታላቅ ብርሃን በውስጡ መላ። ንጉሡም ብርሃኑ ከውጭ እንደሆነ ለማየት ወጣ። ነገር ግን ከውስጥ ሆኖ አገኘው። በውስጧም ብዙ ተአምር ተደረገ።

18 ከእሱም ጋር ሉቃስ የተባለ ጳጳስ ነበር። አቡነ ሉቃስም ከብዙ ጊዜ በኋላ ታህሳስ 28 ቀን አረፈ። በተቀደሰችው በዚህች ቦታም በአንዱ ክፍል ተቀበረ።

19 ከግብጽ አገር የሆነ አንድ ሰውም ነበረ። እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድና ከቅዱሳት ቦታዎች ማለትም ከመካነ ቀራንዮ፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መካነ መቃብር ጎልጎታ፥ ከወንጌላዊው ከማርቆስ መካነ መቃብር፥ ከግብጽና ከእስክንድርያ ገዳማት አፈርና ከዮርዳኖስ ውሃ ያመጣለት ዘንድ ንጉሡን ለመነው። እሱም በፈቃዱ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለዳግማዊ ምኒልክ ላከው። ያሰ ውም ከአንድ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ።

20 ከዚህ ነገር በኋላ ንጉሡ ታመመ። ይጸልዩለትና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሃይማኖትም ቅባት ይቀቡት ዘንድ የቤተ ክርስቲያው ካህናትን ወደ እርሱ ጠራ። ካህናቱም ይጸልዩለትና ቁርባንም ያቀብሉት ነበር።

21 ወእንዘ ከመዝ ይገብር መጽአ ብእሲ ዘይቤሎ ዘፈነዎ ኢየሩሳሌም ወዘከመ በጽሐ በትዕይንተ ምኒልክ ዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ወዘከመ አምጽአ ሎቱ ከሎ ዘይቤሎ። ወፈነወ ንጉሥ ዳግመ እንዘ ይብል ፈኑ ሊተ ፍጡነ። ወፈነወ ሎቱ እንዘ ሀሎ በብሔረ ድማኅ። ወሶበ ርእየ መሬተ እመካናት ቅዱሳት ወማየ ዮርዳኖስ ተፈሥሐ አቢየ ፍሥሐ። ወባረኮ ለእግዚአብሔር ወይቤሎ ይትባረክ እግዚአብሔረ ዘኢከልአኒ ጸሎትየ ወኢያርኀቀ ሣህሎ እምኔየ። እስመ መሐሪ ውእቱ እግዚአብሔር አምላኪየ።

22 ወእምይእቲ ዕለት ተንሥአ እምህየ ወሖረ ደብረ ወርቅ ወአዕረፈ በኀበ ኀደረ በዕለተ አርብ አመ ፫ ለጥር፡፡ ወጾርዎ ሥጋሁ እደው መኳይምናን ወአብጽሕዎ በአንጻሪሃ ለደብረ ማርቆስ ወንጌላዊ። ወወጽኡ ኵሎሙ ካህናት ወዲያቆናት በመንትው ወበማዕጠንት በዕለተ ቀዳም ወተቀበልዎ በክብር ወበማኅሌት እንዘ ይብሉ ሃሌ ሉያ፤ ሃሌ ሉያ፤ ሃሌ ሉያ፤ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት ወውስተ መካነ ዕረፍት ኦ እግዚኦ አዕርፍ ነፍሰ ንጉሥነ ተክለ ሃይማኖት። ወእምዝ ጾርዎ ካህናት ወአብእዎ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወቀበርዎ እደው ጻድቃን ውስተ መቃብር ዘአውቀረ ለርእሱ። ወኮኑ ኵሎሙ ካህናት የአውዱ እንዘ ይብሉ በዜማ ኀዘን ብክይዎ ወላህውዎ እለ ታፈቅርዎ ዬ ዬ ዬ ለተክለ ሃይማኖት።

23 ወዘከመዝ አዕረፈ በ፲፻ወ፰፻ ፺ወ፫ ዓመተ ምሕረት በረከቱ ትኩን ምስለ ወልዱ ወልደ ሩፋኤል ለዓለመ ዓለም አሜን።

24 ሰላም ለተክለ ሃይማኖት ውዱስ፧
ዘተቀጸለ ስምከ አክሊለ ክህነት ወንግሥ፧
ጊዜ እረፍትከ በጽሐ እምኃይለ
ኢየሱስ ክርስቶስ፧
እንተ ተመነይከ ማየ ዮርዳኖስ፧
ወቅድስት መሬት እመካነ ቅዱስ፡፡

21 ይህንም እያደረገ ሳለ ኢየሩሳለም የላከው ሰው ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከዳግማዊ ምኒልክ ከተማ እንደ ደረሰና ያለውን ሁሉ እንዳመጣለት የሚነግረው ሰው መጣ። ንጉሡም በአፋጣኝ ላክልኝ የሚል መልእክት ደግሞ ላከ። በዲማ እያለም ላከለት። የቅዱሳት መካናትን አፈርና የዮርዳኖስንም ውሃ ባየ ጊዜ ደስታ ተሰማው። ጸሎቴን ያልከለከለኝ ይቅርታውንም ከእኔ ያላረቀ እግዚአብሔር ይመስገን አምላኬ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ሲል እግዚአብሔርን አመሰገነው። ከዚህ በኋላ ይህንን ሁሉ እንዲወስዱትና ጎልጎታ ባለው የመቃብር ቦታ እንዲጨምሩት አዘዘ።

22 ከዚህ ቀን ጀምሮ ከዚህ ተነሳ። ወደ ደብረ ወርቅም ሄደ። ባደረበትም እለት ዐርብ ጥር 3 ቀን አረፈ። የታመኑ ሰዎችም አስከሬኑን ተሸክመው በወንጌላዊው በማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ትይዩ አደረሱት። ቅዳሜም ሁሉም ካህናትና ዲያቆናት በመብራትና በማእጠንት ወጥተው ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ ሉያ አቤቱ የንጉሣችንን የተክለ ሃይማኖትን ነፍስ በደስታ ገነትና በዕረፍት ቦታ አሳርፍ እያሉ በክብርና በማኅሌት ተቀበሉት። ወደ ቤተ ክርስቲያንም አስገቡት። ጻድቃኒ ወንዶችም ለራሱ ባሠራው መቃብር ቀበሩት። ሁሉም ካህናት በኀዘን ዜማ ወዮ፥ ወዮ፥ ወዮ፥ ተክለ ሃይማኖትን የምትወዱት አልቅሱለት እያሉ ይዞሩ ነበር።

23 በዚህ ሁኔታ በ1893 ዓ.ም. አረፈ። በረከቱ ከልጁ ከወልደ ሩፋኤል ጋር ትሁን። ለዘላለሙ አሜን።

24 ስምህ የክህነትና የንግሥ ዘውድን የደፋ፥ ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ሰላም ለአንተ ይሁን፡፡
የተመሰገንክ የዮርዳኖስ ውሃና፧
ከቅድስት ቦታ የሆነችው ቅድስት አፈር፧
በእረፍትህ ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ደረሰ።

የአዲስ አበባ ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ስንክሳር ጥር 3

21 ወእንዘ ከመዝ ይገብር መጽአ ብእሲ ዘይቤሎ ዘፌነዎ ኢየሩሳሌም ወዘከመ በጽሐ በትዕይንተ ምኒልክ ዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ወዘከመ አምጽአ ሎቱ ከኈሎ ዘይቤሎ። ወፈነወ ንጉሥ ዳግመ እንዘ ይብል ፈኑ ሊተ ፍጡነ። ወፈነወ ሎቱ እንዘ ሀሎ በብሔረ ድማኅ። ወሶበ ርእየ መሬተ እመካናት ቅዱሳት ወማየ ዮርዳኖስ ተፈሥሐ አቢየ ፍሥሓ። ወባረኮ ለእግዚአብሔር ወይቤሎ ይትባረክ እግዚአብሔረ ዘኢከልአኒ ጸሎትየ ወኢያርኀቀ ሣህሎ እምኔየ። እስመ መሐሪ ውእቱ እግዚአብሔር አምላኪየ።

22 ወእምይእቲ ዕለት ተንሥአ እምህየ ወሖረ ደብረ ወርቅ ወአዕረፈ በኀበ ኀደረ በዕለተ አርብ አመ ፫ ለጥር፡፡ ወጾርዎ ሥጋሁ እደው መ፡ኅይምናን ወአብጽሕዎ በአንጻሪሃ ለደብረ ማርቆስ ወንጌላዊ። ወወጽኡ ኲሎሙ ካህናት ወዲያቆናት በመኀትው ወበማዕጠንት በዕለተ ቀዳም ወተቀበልዎ በክብር ወበማኅሌት እንዘ ይብሉ ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሉያ፣ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት ወውስተ መካነ ዕረፍት ኦ እግዚኦ አዕርፍ ነፍሰ ንጉሥነ ተክለ ሃይማኖት። ወእምዝ ጾርዎ ካህናት ወአብእዎ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ወቀበርዎ እደው ጻድቃን ውስተ መቃብር ዘአውቀረ ለርእሱ። ወኮኑ ኲሎሙ ካህናት የአውዱ እንዘ ይብሉ በዜማ ኅዘን ብክይዎ ወላህውዎ እለ ታፈቅርዎ ዬ ዬ ዬ ለተክለ ሃይማኖት።

23 ወዘከመዝ አዕረፈ በ፲፻ወ፰፻ ፺ወ፫ ዓመተ ምሕረት በረከቱ ትኩን ምስለ ወልዱ ወልደ ሩፋኤል ለዓለመ ዓለም አሜን።

24 ሰላም ለተክለ ሃይማኖት ውዱስ፤
ዘተቀጸለ ስምከ አክሊለ ክህነት ወንግሥ፤
ጊዜ እረፍትከ በጽሐ እም፡ኅይለ
ኢየሱስ ክርስቶስ፤
እንተ ተመነይከ ማየ ዮርዳኖስ፤
ወቅድስት መሬት እመካን ቅዱስ፡፡

21 ይህንም እያደረገ ሳለ ኢየሩሳለም የላከው ሰው ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከዳግማዊ ምኒልክ ከተማ እንደ ደረሰና ያለውን ሁሉ እንዳመጣለት የሚነግረው ሰው መጣ። ንጉሡም በአፋጣኝ ላክልኝ የሚል መልእክት ደግሞ ላከ። በዲማ እያለም ላከለት። የቅዱሳት መካናትን አፈርና የዮርዳኖስንም ውሃ ባየ ጊዜ ደስታ ተሰማው። ጸሎቴን ያልከለከለኝ ይቅርታውንም ከእኔ ያላረቀ እግዚአብሔር ይመስገን አምላኬ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ሲል እግዚአብሔርን አመሰገነው። ከዚህ በኋላ ይህንን ሁሉ እንዲወስዱትና ጎልጎታ ባለው የመቃብር ቦታ እንዲጨምሩት አዘዘ።

22 ከዚህ ቀን ጀምሮ ከዚህ ተነሳ። ወደ ደብረ ወርቅም ሄደ። ባደረበትም እለት ዐርብ ጥር 3 ቀን አረፈ። የታመኑ ሰዎችም አስከሬኑን ተሸክመው በወንጌላዊው በማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ትይዩ አደረሱት። ቅዳሜም ሁሉም ካህናትና ዲያቆናት በመብራትና በማእጠንት ወጥተው ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ ሉያ አቤቱ የንጉሣችንን የተክለ ሃይማኖትን ነፍስ በደስታ ገነትና በዕረፍት ቦታ አሳርፍ እያሉ በክብርና በማኅሌት ተቀበሉት። ወደ ቤተ ክርስቲያንም አስገቡት። ጻድቃኊ ወንዶችም ለራሱ ባሠራው መቃብር ቀበሩት። ሁሉም ካህናት በኀዘን ዜማ ወዮ፥ ወዮ፥ ወዮ፥ ተክለ ሃይማኖትን የምትወዱት አልቅሱለት እያሉ ይዞሩ ነበር።

23 በዚህ ሁኔታ በ1893 ዓ.ም. አረፈ። በረከቱ ከልጁ ከወልደ ሩፋኤል ጋር ትሁን። ለዘላለሙ አሜን።

24 ስምህ የክህነትና የንግሥ ዘውድን የደፋ፥
ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ሰላም ለአንተ ይሁን፡፡
የተመሰገንክ የዮርዳኖስ ውሃና፣
ከቅድስት ቦታ የሆነችው ቅድስት አፈር፤
በእረፍትህ ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ
ደረሰ።

ፔቡቃ፡፡
ፊኘቋ፥

የአዲስ አበባ ብርሃናተ ዓለም
ወጳውሎስ ስንክሳር ጥር 3

ቃቡቃ።
ሀኖሆቆ